# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

እሁድ 83ኛ ዓመት ቁጥር 139 ጥር 19 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




# «የአመራር መተካካቱ ብልጽግና ‘በአብዮት’ ሳይሆን በሪፎርም እንደሚያምን ትልቅ ማሳያ ነው»

የብልጽግና ፓርቲ ፕሬዚዳንት

ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- የአቶ ደመቀ መኮንን ለረጅም ዓመታት ሀገራቸውንና ፓርቲያቸውን አገልግለው በክብር መሸኘት ብልጽግና ‘በአብዮት’ ሳይሆን በሪፎርም እንደሚያምን ትልቅ ማሳያ መሆኑን የብልጽግና ፓርቲ ፕሬዚዳንት ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር) ገለጹ።

ፕሬዚዳንቱ የአቶ ደመቀ መኮንንን የክብር ሽኝት በሚመለከት ለፓርቲው ማዕከላዊ ኮሚቴ በሰጡት ማብራሪያ እንዳሉት፤ አቶ ደመቀ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ረዘም ላለ ጊዜ በርካታ የመንግሥት ኃላፊነት ወስደው የማገልገል ዕድል አግኝተዋል። ይህም ብልጽግና በሪፎርም እንጂ ‘በአብዮት’ እንደማያምን ትልቅ ማሳያ ሆኖ የሚያገለግል ነው።

በቀደሙት ጊዜያት የነበሩ መሪዎች ይህን እንዳላገኙ

“ የአመራር መተካካቱ...ወደ ገጽ 5 ዞሯል

# ኢትዮጵያ በዲፕሎማሲው መስክ ተደማጭ እንድትሆን ሚሲዮኖች የድርሻቸውን ሊወጡ ይገባል

## - ዓመታዊው የሚሲዮን መሪዎች ስብሰባ ተጠናቀቀ

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ በዲፕሎማሲ መስክ ቀዳሚና ተደማጭነቷ የጎላ እንድትሆን ሚሲዮኖች የድርሻቸውን ሊወጡ እንደሚገባ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አስታወቀ። ዓመታዊው የሚሲዮን መሪዎች ስብሰባ ትናንት ተጠናቋል።

በማጠቃለያ መርሐ ግብሩ የተገኙት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን አምባሳደሮች በቀጣይ ጊዜያት በሚያከናውኗቸው ተግባራት ዙሪያ መመሪያ ሰጥተዋል።

በወቅቱ ለመገናኛ ብዙኃን መግለጫ የሰጡት የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ አምባሳደር መለስ ዓለም (ዶ/ር) እንደገለጹት፤ በተለያዩ ሀገራት የኢትዮጵያን



ብሔራዊ ጥቅም ለማስጠበቅ የተወከሉ አምባሳደሮች የተሰጣቸውን ኃላፊነት በአግባቡ እንዲወጡ መመሪያ ተሰጥቷል።

በተለያዩ ሀገራት የተሰማሩ የኢትዮጵያ አምባሳደሮች አውዱ የሰፋ የዲፕሎማሲ እንቅስቃሴ ማከናወን እንደሚጠበቅባቸው

ኢትዮጵያ በዲፕሎማሲው...ወደ ገጽ 5 ዞሯል



# በክልሉ ከሀገር ውስጥ ጎብኚዎች የተገኘው 800 ሚሊዮን ብር በኢኮኖሚው ውስጥ ተንቀሳቅሷል

## -የሀላላ ኬላ ሎጅ ሥራ ከጀመረ በኋላ የቱሪስት ቁጥር ጨምሯል

**መዓዛ ማሞ**

አዲስ አበባ፡- በመንፈቅ ዓመቱ ከሀገር ውስጥ ጎብኚዎች 800 ሚሊዮን ብር ወደ ኢኮኖሚው ውስጥ መንቀሳቀሱን በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል ቱሪዝም ቢሮ ገለጸ፡፡ የሀላላ ኬላ ሎጅ ሥራ ከጀመረ በኋላ ከፍተኛ የቱሪስት ቁጥር ወደ ክልሉ መምጣት መጀመሩም ተጠቁሟል፡፡

የደቡብ ምዕራብ ክልል ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ አቶ ፋንታሁን ብላቴ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በመንፈቅ ዓመቱ ክልሉን ከሚጎበኙ የሀገር ውስጥ ጎብኚዎች አንድ ቢሊዮን ብር ኢኮኖሚው

በክልሉ ከሀገር...ወደ ገጽ 5 ዞሯል















«ሀገራዊ ምክክሩ የሀገራችንን የወደፊት ዕጣ ፈንታ ስለሚወስን በንቃት ልንሳተፍበት ይገባል»

\- ምሁራን

ገጽ 5







# በክልሉ ከሌማት ትሩፋት ከሁለት ነጥብ አንድ ቢሊዮን ሊትር በላይ የወተት ምርት ተገኘ

## - ከ206 ሺህ ቶን በላይ የዶሮ ስጋና የዓሣ ምርት ማግኘት ተችሏል

**ማህሌት ብዙነህ**

አዲስ አበባ፡- በኦሮሚያ ክልል በጀት ዓመቱ ስድስት ወራት ውስጥ በሌማት ትሩፋት መርሀ ግብር ከሁለት ነጥብ አንድ ቢሊዮን ሊትር በላይ የወተት ምርት መገኘቱን የክልሉ ግብርና ቢሮ አስታወቀ። ከ206 ሺህ ቶን በላይ የዶሮ ስጋና የዓሣ ምርት ማግኘት መቻሉንም ተመልክቷል።

በኦሮሚያ ግብርና ቢሮ የእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ እና ልማት ዳይሬክተር አቶ ደምሴ ኩምሳ ለኢፕድ እንደገለጹት፤ በክልሉ እየተተገበረ ከሚገኘው ሌማት ትፋት መርሀግብር በበጀት ዓመቱ ከሦስት ቢሊዮን 364 ሚሊዮን 192 ሺህ ሊትር በላይ (3,364,192,806 ) የወተት ምርት ለማግኘት ታቅዶ በግማሽ ዓመቱ በክልሉ ከሌማት ትሩፋት ከ 2 ነጥብ 1 ቢሊዮን ሊትር በላይ የወተት ምርት ተገኝቷል፡፡

በስድስት ወራት ውስጥም ሁለት ቢሊዮን 18 ሚሊዮን 515 ሺህ 683 ሊትር የወተት ምርት ለማግኘት ታቅዶ ሁለት ቢሊዮን 167 ሚሊዮን 662 ሺህ 410 ሊትር የተገኘ መሆኑን ገልጸው፤ ይህም ከእቅድ በላይ መፈጸም መቻሉንም አስታውቀዋል፡፡

የወተት ልማት መርሀ ግብር ከ201 ሺህ 480 በላይ አርሶ አደሮች ተሳታፊ መሆናቸውን ገልጸው፤ ከአንድ ሺህ 679 በላይ ወተት መንደሮችን ማደራጀት መቻሉን ተናግረዋል፡፡



የሌማት ትሩፋት ይፋ ከሆነበት ከጥቅምት ወር 2015 ዓ.ም ጀምሮ እስካሁን ድረስም ሦስት ሺህ 914 የወተት መንደር በመለየት እየተተገበረ እንደሆነ አቶ ደምሴ አስታውቀዋል፡፡

በመርሀ ግብሩ በዶሮ ልማት ሥራ በግማሽ ዓመት ውስጥ አንድ ሺህ 654 መንደሮችን በመለየት 165 ሺህ በላይ አርሶ አደሮችን ማሳተፍ ተችሏል፡፡ በዚህም 46 ሺህ 716 ቶን የዶሮ ስጋ ለማምረት ታቅዶ 49 ሺህ 252 ቶን የዶሮ ስጋ ማምረት መቻሉን ጠቁመዋል። ከአንድ ቢሊዮን 295 ሚሊዮን 016 በላይ የእንቁላል ምርት መገኘቱንም ገልጸዋል፡፡

አቶ ደምሴ እንደገለጹት፤ በዓሣ ልማት 97 ሺህ 765 ቶን ዓሣ ለማምርት ታቅዶ 157ሺህ 258 ቶን ዓሣ ማምረት መቻሉን አመልክተው፤ በዚህም በ125 መንደሮች ሁለት ሺህ 500 ተሳታፊ አርብቶ አደሮች በመለየት የተሠራ ነው ብለዋል፡፡

54 ሺህ ሦስት መቶ ቶን የማር ምርት በበጀት ዓመቱ ግማሽ ዓመት ማምረት ተችሏል ያሉት አቶ ደምሴ፤ ይህንንም በ489 የማር መንደር የሚገኙ 9ሺህ 780 አርብቶ አደሮች ተሳታፊ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

በሌማት ትሩፋት ሥራው ላይ በበጀት እጥረት ምክንያት ዘርፉን በስፋት ለማስተዋወቅ ብሎም ለድጋፍና ክትትል ሥራ ተግዳሮች እንደሆነ አስታውቀው፤ የግብአት ጥራትና አቅርቦት ማነስ እና በቂ የገበያ ትስስር አለመኖር የሚስተዋሉ ተግዳሮቶች መሆናቸውን ጠቅሰዋል፡፡

የዘንድሮ ግማሽ ዓመት የሌማት ትሩፋት አፈጻጸም ካለፈው ሙሉ ዓመት ጋር ሲነጻጸር ብልጫ እንዳለው ገልጸው፤ ይህ እጥፍ እድገትም በመንግሥት ትኩረት ተሰጥቶት እየተሠራ እንደሆነ ማሳያ ነው ብለዋል፡፡

በመርሀ ግብሩም ሰፊ ቁጥር ያለው ኅብረተሰብ በማሳተፍ ከሥራ ዕድል እና ከገቢ ምንጭነት ባለፈ የክልሉን የምግብ ዋስትና በማረጋገጥ በኩል ጉልህ ሚና እየተጫወተ ነው ሲሉ ተናግረዋል፡፡



# አገልግሎቱ በአርባ ምንጭ ከተማ ለሚገኙ ለተለያዩ ተቋማት የመጽሐፍት ድጋፍ ሊያደርግ ነው

**ሞገስ ጸጋዬ**

አርባ ምንጭ፡- በአርባ ምንጭና በጨንቻ ከተማ ለሚገኝ የተለያዩ ተቋማት ከአንድ ነጥብ 3 ሚሊዮን ብር በላይ ዋጋ ያላቸው የመጽሐፍት ድጋፍ ሊያደርግ መሆኑን የኢትዮጵያ ቤተ መዛግብትና ቤተ-መጻሕፍት አገልግሎት አስታወቀ።

የኢትዮጵያ ቤተ መዛግብትና ቤተ-መጻሕፍት አገልግሎት ከአርባምንጭ ዩኒቨርሲቲና ከጋሞ ዞን ባህልና ቱሪዝም መምሪያ ጋር በመተባበር «አርባ ምንጭ ታንብብ» በሚል መሪ ቃል የተዘጋጀ የንባብ ሳምንት ተከፈተ። የንባብ ሳምንቱ እስከ ጥር 21 ቀን የሚቆይ ይሆናል።

በመርሐግብሩ ላይ ንግግር ያደረጉት የኢትዮጵያ ቤተ መዛግብትና ቤተ-መጻሕፍት አገልግሎት የዋና ዳይሬክተር ተወካይ አቶ ያሬድ ተፈራ እንደገለጹት፣ በአርባ ምንጭ ከተማ እየተካሄደ ያለው የንባብ ሳምንት የንባብ ባህልን በማሳደግ የሕዝብ፣ የማረሚያ ቤቶችና የትምህርት ቤቶች ቤተመጻሕፍትን ለማጠናከር ከዛሬ ጀምሮ የመጽሐፍት ድጋፍ ሊያደርግ ነው።

አገልግሎቱ በሀገሪቱ ያሉ ማረሚያ ቤቶችን የመጽሐፍት ድጋፍ እያደረገ ነው ያሉት አቶ ያሬድ፣ በንባብ ሳምንቱ በአርባ ምንጭ የወጣት ማዕከላት፣ የሕዝብ ቤተመጻሕፍት፣ ስድስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፣ ማረሚያ ቤቶች፣ በጨንቻ ዙሪያ የሚገኝ ሁለት ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፣ የጨንቻ ወጣት ማዕከልና የጨንቻ ከተማ ማረሚያ ቤት የመጽሐፍት ድጋፍ የሚደረግላቸው ተቋማት መሆናቸውን ጠቅሰዋል።

መጻሕፍቱ አንድ ሚሊዮን 364ሺህ የሚገመት ገንዘብ ወጥቶባቸው የተገዙ መሆናቸውን አመልክተው፤ ዛጐል የመጽሐፍ ባንክ 200 መጽሐፍት በድጋፍ መልክ ማበርከቱን ገልጸዋል።

የንባብ ሳምንት ቀጣይነት እንዲኖረው በስጦታ መልክ የሚበረከቱ መጽሐፍት ለተጠቃሚ ተደራሽ እንዲሆን አሳስበዋል። የመጽሐፍ ድጋፉ የተሻለ ትውልድ ለመገንባት ይረዳል ነው ያሉት።

የንባብ ክበባትን በመመስረት የንባብ ባህል በማኅበረሰቡ ተደራሽ እንዲሆን እየተደረገ መሆኑን ገልጸው፤ የንባብ ሳምንቱ የተሳካ እንዲሆን አንጋፋና ወጣት ደራሲያን ልምዳቸውን ለአንባቢያንና ተማሪዎች ተደራሽ እያደረጉ ነው ብለዋል አቶ ያሬድ።

የአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዶክተር ዳምጠው ዳርዛ እንደገለጹት፣ አንባቢ ትውልድ ችግሮችን በብልሃት የመፍታት አቅምን ይጐናጸፋል። እንዲሁም ለራሱ፣ ለሀገርና ለማኅበረሰብ ከፍ ያለ አስተዋጽኦ ያበረክታል።

ንባብ ለሁለተናዊ እድገት ትልቅ አስተዋጽኦ አለው ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ ማንበብን የሚወድ ትውልድ ለጥበብ ቅርብ ነው። እንደ ሀገር የሚከሰቱ ችግሮችን በንግግርና በውይይት የመፍታት አቅም ይኖረዋል። ኢትዮጵያውያን ታሪካቸውን በትክክል በመገንዘብና ሰንዶ በመጠቀም ለሀገር እድገት የራሳቸውን ሚና ሊወጡ እንደሚገባ ገልጸዋል።

የአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ በእውቀት የተገነባ ትውልድ እንዲገነባ አበክሮ እየሠራ መሆኑን አውስተው፤ ለሽያጭ የቀረቡት መጽሐፍት ስለ አርባ ምንጭ ታሪክ የሚያወሱ መሆናቸውን ፕሬዚዳንቱ ገልጸዋል።

# በ23 ከተሞች የሳኒቴሽን ፕሮጀክቶች ግንባታ ለመጀመር በጨረታ ሂደት ላይ ነው

**መስከረም ሰይፉ**

አዲስ አበባ፡- በ23 ከተሞች የሳኒቴሽን ፕሮጀክቶች ግንባታ ለመጀመር ጥናቱ ተጠናቆ በጨረታ ሂደት ላይ እንደሚገኝ የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

በውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር የሳኒቴሽን መሠረተ ልማት መሪ ሥራ አስፈጻሚ አቶ ኑረዲን መሐመድ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ጤናማ ማኅበረሰብ ለመፍጠር የሳኒቴሽን ፕሮጀክቶች ግንባታ ትልቅ ሚና አለው፡፡ በ23 ከተሞች የሳኒቴሽን (የቆሻሻ ፍሳሽ ማጣሪያ ጣቢያዎች) ፕሮጀክቶች ግንባታ ለመጀመር በጨረታ ሂደት ላይ ይገኛል፡፡

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በ23 ከተሞች የሳኒቴሽን ፕሮጀክቶች ሙሉ ጥናት ተጠናቆ ግንባታ ለመጀመር በጨረታ ሂደት ላይ ይገኛል ያሉት አቶ ኑረዲን፤ በእነዚህ ፕሮጀክቶች የሚካተቱ ከአንድ ሺ በላይ የሕዝብና የጋራ መጸዳጃ ቤቶች ግንባታቸው ከ50 በመቶ መጠናቀቃቸውን ተናግረዋል፡፡

መጸዳጃ ቤቶችን ከመገንባት ባለፈ ከቤት የሚወጣ ፍሳሽ ቆሻሻዎችን ባግባቡ ተጣርቶ መልቀቅ ካልተቻለ ማኅበረሰቡ ጤና ላይ አሉታዊ ተጽእኖ የሚያሳድር መሆኑን ገልጸው፤ እነዚህ የሳኒቴሽን ፕሮጀክቶችም ከየቤቱ የሚወጡ ፍሳሽ ቆሻሻዎችን አጣርቶ ለማስወገድ ያስችላሉ ብለዋል፡፡

ፕሮጀክቶቹ የ505 ሚሊዮን ዶላር በጀት የተያዘላቸው መሆኑን አመልክተው፤ 60 ሚሊዮኑ በአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ሲሸፈን ቀሪው ወጪ በዓለም ባንክ ድጋፍ የሚሸፈን መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ፕሮጀክቶቹ በተለያየ ምዕራፍ የሚገነቡ ሲሆን የመጀመሪያው ምዕራፍ ግንባታም ቢያንስ እስከ 10 ዓመት ማገልገል የሚችል የቆሻሻ ፍሳሽ ማጣሪያ ጣቢያን እንደሚያካትትም ጠቁመዋል፡፡



**አቶ ኑረዲን መሐመድ**

በ22 ከተሞች ላይ የሚገነቡት ፕሮጀክቶች ከአንድ ዓመት እስከ አንድ ዓመት ከመንፈቅ የሚጠናቀቁ መሆናቸውን ጠቁመው፤ በአዲስ አበባ ከተማ በሃያት ሲኤምሲ አካባቢ የሚገነባው ፕሮጀክት እስከ 3 ዓመት ጊዜ የሚፈጅ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

ከዚህ ቀደም በአዲስ አበባ ሦስት የሳኒቴሽን የፍሳሽ ማጣሪያዎች ቢኖሩም አሁን ያለውን የከተማ ሕዝብ እድገት የማያስተናግዱና የቆዩ በመሆናቸው በሚፈለገው ልክ አገልግሎት እየሰጡ አለመሆናቸውን አውስተው፤ አሁን የሚገነቡት የሳኒቴሽን ፕሮጀክቶች ይህንን ችግር ይቀርፋሉ ተብሎ እንደሚታሰብ አብራርተዋል፡፡

አቶ ኑረዲን የሳኒቴሽን ፕሮጀክቶች ጤና ማኅበረሰብን በመፍጠር፣ ሚናቸው ትልቅ ቢሆንም ለሳኒቴሽን ያለው ግንዛቤ አነስተኛ በመሆኑ ብዙ ሥራዎች መሥራት አለመቻሉን ተናግረዋል፡፡ ሳኒቴሽን ፕሮጀክቶች ለመገንባትም ቦታ አለማግኘትና የፋይናንስ እጥረት የዘርፉ ዋና ዋና ችግሮች መሆናቸውን ጠቅሰዋል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## የአርብቶ አደሩን አካባቢ ልማት በአርብቶ አደሩ እምቅ ሀብት!

የምሥራቅ አፍሪካ ሀገራት ከሚታወቁባቸው ግንኙነቶቻቸው መካከል ድንበር ሳይወስናቸው በሰፊ ስፍራዎች ላይ በሚኖሩት አርብቶ አደሮቻቸው መካከል ያለው ጥብቅ ትስስር ይጠቀሳል፡፡ አርብቶ አደሮቹ ከፍተኛ መጠን ባለው የእንስሳት ሀብታቸው በእጅጉ ይታወቃሉ፡፡

አርብቶ አደሮቹ ለእንስሳቶቻቸው ሲሉ ከቦታ ቦታ የሚያደርጉት እንቅስቃሴ ከአንዱ ሀገር ወደ አንዱ ሀገር በነጻነት እንዲገቡና እንዲወጡ ሲያደርጋቸው ኖሯል፡፡ ይህ ምንም አይነት ቪዛ ሳያስፈልጋቸው እንደ ልብ ከሀገር ሀገር የሚንቀሳቀሱበት መንገድ የአርብቶ አደሮቹ ብቻ ሳይሆን የምሥራቅ አፍሪካም መለያና ትልቅ አቅም ተደርጎ መወሰድ ይኖርበታል፡፡ ይህ ጥብቅ ግንኙነት የፖለቲካ ውሳኔ ከሚፈጥረው ትስስር በላይ በጠንካራ የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት ላይ የተመሰረተ፣ በቀላሉ የማይናወጥና ዘመናትንም የተሻገረ ነው፡፡

አርብቶ አደሮቹ የአካባቢው ትልቅ አቅም የሆነውን የእንስሳት ሀብት በራሳቸው መንገድ እያለሙ ይገኛሉ፡፡ በእዚህ ሀብት ልማት ላይ የአካባቢው ሀገሮች ብዙም የጨመሩት እሴት የለም፤ የአርብቶ አደሩ ከብቶች ጤና የሚጠበቅበት ሁኔታ ብዙም ጠንካራ ባለመሆኑ፤ አርብቶ አደሩ የከብት ግብይት የሚፈጸምበት መንገድ ዛሬም እንደ ጥንቱ በቁሳቁስ ልውውጥ የሚካሄድበት /ባርትሬድ/ ሁኔታ፣ አካባቢው ለድርቅ ያለው ተጋላጭነት ከፍተኛ መሆኑም በዘርፉ ላይ ብዙ አለመሰራቱን ያመለክታሉ፡፡

መንግሥታት ለአካባቢውና ለማኅበረሰቡ ሲሰጡ የቆዩት ትኩረት አናሳ በመሆኑ በአካባቢው ድርቅ፣ ጎርፍ እና የእንስሳት በሽታ ደጋግሞ ይከሰታል፡፡ ባለፉት ዓመታት በድርቅ ሳቢያ በኢትዮጵያ የአርብቶ አደር አካባቢዎች ያለቁት ከብቶች ብዛት የችግሩን አሳሳቢነት ቁልጭ አድርጎ ያሳያል፡፡ አርብቶ አደሩ ከእንስሳቶቹ የሚያገኘው ተጠቃሚነት በመሰረተ ልማትና በገበያ እጦት፣ በጤና መታወክና በህገወጥ ግብይት ሳቢያ እዚህ ግባ የማይባል ሆኖ ኖሯል፡፡ የመሰረተ ልማት እጦቱ የአርብቶ አደሩ የእንስሳት ሀብት እንዲባክን እያደረገው ነው፡፡

እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ሀገራት ለአርብቶ አደሩ ትኩረት ሰጥተው መስራት የጀመሩ ቢሆንም፣ አካባቢው ካለው እምቅ አቅም፣ አርብቶ አደሩ ከሚገኝበት ዝቅተኛ ህይወት አኳያ ሲታይ ብዙ ተሠርቷል የሚያሰኝ አይደለም፡፡ የአካባቢውን በርካታ ትላልቅ ወንዞች ማልማት ባለመቻሉ አርብቶ አደሩ ለእንስሳቶቹ ውሃ ፍለጋ፣ በዚህ ሀብት መኖ በማልማት ከብቶቹን መመገብ የሚቻልበት ዕድል እያለ ዛሬም እንደ ጥንቱ ከአካባቢ አካባቢ፣ ከሀገር ሀገር መንከራተቱን ቀጥሏል፡፡

አርብቶ አደሩን ከዚህ አይነቱ ችግር በማውጣት ሕይወቱን ለመቀየር፣ የአካባቢው ሀገሮችም ከዚሁ አካባቢ ሀብት በሚገባ ተጠቃሚ የሚሆኑበትን መንገድ ለመፍጠር እንደ ሀገርም እንደ አካባቢም የተጀመሩ ጥረቶች መጠናከር ይኖርባቸዋል፡፡

ለእዚህም የአካባቢው አርብቶ አደሮች የቆየ ትስስር ያለምንም ቪዛ ከሀገር ሀገር የሚገቡበትና የሚወጡበት መንገድ ፣ አካባቢያቸውን የሚያስተዳድሩበት ሁኔታ አካባቢውን ለመለወጥ ለሚደረገው ጥረት ትልቅ ግብአት ተደርጎ መወሰድ ይኖርበታል፡፡ ልማቱን በጋራ አስተሳስሮ ለማካሄድም ከፍተኛ ፋይዳ ይኖረዋል፡፡

ከዚህ አኳያ ከትናንት በስቲያ በሚሊኒየም አዳራሽ የተጀመረው የምሥራቅ አፍሪካ አርብቶ አደሮች ኤክስፖ ትልቅ ስፍራ ሊሰጠው ይገባል፡፡ የምሥራቅ አፍሪካ ሀገራትን በኢኮኖሚ በማስተሳሰር የጋራ ተጠቃሚነትን ማስፈን የኢትዮጵያ የምንጊዜም ፍላጎትና ጥረት መሆኑን መድረኩን የከፈቱት የኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባኤ አቶ ታገሰ ጫፎ አስታውቀዋል፡፡

‹‹ኤክስፖው ትስስራችን ምን ያህል የጠነከረ፣ አጥርና ድንበር የሌለን ወንድማማቾችና እህትማማቾች መሆናችንን በግልፅ የሚያሳይ ነው›› ያሉት አፈ ጉባኤው፣ ይህንን ትልቅ እሴት በኢኮኖሚ በማስተሳሰር የጋራ ተጠቃሚነትን ማስፈን የኢትዮጵያ የምንጊዜም ፍላጎትና ጥረት መሆኑንም አመልክተዋል፡፡

‹‹አርብቶ አደሩ አጥርም ድንበርም የለውም፤ ይህም የቀጣናችንን ትስስር ለማጠናከር፣ አብሮ ለመበልፀግ እንዴት መጓዝና መደመር እንዳለብን ብዙ ይነግረናል›› ሲሉ የተናገሩትም የአርብቶ አደሩን አካባቢ ለማልማት ከራሱ ከአርብቶ አደሩ ህይወት ብዙ ትምህርት መቅሰም እንደሚቻል ያስገነዝባል፡፡

በእርግጥም ይህን የአርብቶ አደሩን የቆየ እሴት በመጠቀም አካባቢውን ማልማት ይቻላል፡፡ አካባቢው በቂ ሀብት አለው፤ አብሮ መልማት የሚያስችል ዘመናነትን የተሻገረ በቂ አቅምም አለው፡፡ ይህን ማልማት የሚቻልበትን ሁኔታ በመፍጠር አካባቢውን በድርቅና በመሳሰሉት ችግሮች በቀላሉ ከሚጠቃበት ሁኔታ ማውጣት ፣ የአካባቢውን ሀገሮችም ተጠቃሚ ማድረግ ይቻላል፡፡ ምሥራቅ አፍሪካን በንግድ ለማስተሳሰር እየተሞከረ ያለበትን መንገድ በመጠቀምም እንዲሁ አካባቢው በቂ ገበያ እንዲኖረው በማድረግ ከእንስሳት ሀብቱ ሽያጭ በሚገባ ተጠቃሚ እንዲሆን ማድረግ ይቻላል፡፡

ለእዚህም የአርብቶ አደሩን አካባቢ ለማልማት የሚደረገውን ጥረት ይበልጥ ማጠናከር፣ እንደ ቀጣናም መሰል መድረኮችን ቶሎ ቶሎ በማዘጋጀት ከመድረኮቹ የተገኙ ሃሳቦችን ወደ ተግባር በመቀየር ላይ መስራት ያስፈልጋል፡፡

የአርብቶ አደሩን አካባቢ በአካባቢው ሀብት ማልማት ይቻላል፡፡ የአካባቢው ሀብትና የአርብቶ አደሩ ልምድና ተሞክሮ ለእዚህ ትልቅ አቅም በመሆን ያገለግላሉና፡፡ በእዚህ ትልቅ ሀብት ላይ ጥቂት ሀብት መጨመር ነው የሚያስፈልገው፡፡ ይህ ሲሆን አርብቶ አደሮቹን፣ ሀገራቱንና ሕዝባቸውን ብሎም ቀጣናውን ይበልጥ በማልማት ተጠቃሚ ማድረግ ይቻላል!


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ሕግ እና የሕግ የበላይነት

በቁምላቸው አበበ ይማም(ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

በዚሁ አምድ ህገ ወጥ ንግድን ወይም ኮንትሮባንድን በተመለከተ ለመጫጫር ሳወጣ ሳወርድ፣ ችግሩ እንዲህ ሊስፋፋ የቻለው በተለያዩ ምክንያቶች ቢሆንም ዋናው ግን የሕግ የበላይነት ሙሉ በሙሉ አለመረጋገጡ ነው ብዬ አሰብሁ።እንደ ሀገር ያለንበት አጠቃላይ ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ቀውስ ውስጥም ያልተከበረ ያልተረጋገጠ የሕግ የበላይነት ክፍተት እንዳለ ተረዳሁ።እንደ ዜጋ በሁሉም ተቋሞቻችን የሕግ የበላይነት ቢረጋገጥ ኖሮ ዛሬ ሀገራችን መስቀለኛ መንገድ ላይ አትገኝም ነበር የሚል ቁጭትም ፈጠረብኝ።

በዚህ ቁጭት ላይ ሆኜ ስለ የህግ የበላይነት ምንነት ይበልጥ ለመረዳት በድረ ገጽ ሳስስና በጎግል "ስጎለጉል" ኃይለማርያም ይርጋ የተባሉ የህግ ሊቃውንት ጋር ልክ በእውን የተገናኘሁ ያህል "ቨርቹዋ" ተገጣጠምሁ። በማስከተልም በምናብ ለመሆኑ የሕግ የበላይነት ማለት ምን ማለት ነው ስል ጠየቅኋቸው።በነገራችን ላይ የምናብ ቃለ መጠይቅ የማድረግ ሀሳብ የመጣልኝ ተወዳጁ የCNN የGPS አዘጋጅና የዓለም አቀፍ ግንኙነት ሊቅ ፋሪድ ዘካሪያ ከሰሜን ኮሪያው መሪ ኪም ጆንግ ኡን ጋር በአካል ተገናኝቶ ፊት ለፊት ቃለ መጠይቅ ማድረግ እንደማይችል ሲያውቅ ምናባዊ ቃለ መጠይቅ ለማድረግ ተነሳ።

ጥያቄዎቹን ካወጣ በኋላ ለእያንዳንዱ ጥያቄ ኪም ምን ብሎ ሊመልስለት እንደሚችል በምናብ እያሰበ መልሱን ዘረዘረ።ጠያቂም መላሺም ሆነ።እንደ ሀገራችን ጋዜጠኞች ለማነጋገር ያደረግነው ተደጋጋሚ ሙከራ ሳይሳካ ቀርቷል ከሚለው የጨረተ "Clichy" አባባል ይሻላል። እኔም ከአቶ ኃይለማርያም ጋር እንዲህ በምናብ ለቃለ መጠይቅ ተቀመጥሁ። የኔው ከፋሪድ የሚለየው ጠያቂ እንጂ መላሽ አለመሆኔ ነው።ጥያቄዎቹን የሚመልሱት ሊቅ ሲኖሩ በአካል መገናኘት ያልቻልሁት እኔ ስለሆንሁ ከፋሪዱ በፍጹም ይለያል።መልሶችም ከእኔ ምናብ የፈለቁ ሳይሆኑ የአቶ ኃይለማርያም ናቸው።

የሕግ የበላይነት ሲባል

በኢፌዴሪ ሕገመንግሥት መግቢያ ላይ“ በሀገራችን ኢትዮጵያ ውስጥ ዘላቂ ሰላም፣ ዋስትና ያለው ዲሞክራሲ እንዲሰፍን፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እድገታችን እንዲፋጠን.....በሕግ የበላይነት ላይ የተመሰረተ አንድ ፖለቲካል ኢኮኖሚ ማህበረሰብ ለመገንባት..” በሚል የሕግ የበላይነት ለሀገራችን ግንባታ ወሳኝ እንደሆነ ይገልፃል፡፡ ሆኖም ግን የሕግ የበላይነት የሚለው ቃል በህገ መንግሥቱም ሆነ በሌሎች ዓለም አቀፍ የቃል ኪዳን ሰነዶች ቢጠቀስም ስምምነት ላይ የተደረሰበት አንዳች ትርጉም ሲሰጠው አይስተዋልም፡፡

ከመዝገበ ቃላት ትርጉም ይልቅ የተሟላ ግንዛቤ ይረዳን ዘንድ ዊሊያም ጋርድነር የተባለ የህግ ምሁር “THE HISTORY AND ELEMENTS OF THE RULE OF LAW” በተሰኘው መጽሐፍ ላይ ያስቀመጠውን ትርጉም እና የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ዳይሬክተር በ2014 እኤአ ለፀጥታው ምክር ቤት ባቀረበው ሪፖርት ላይ ለህግ የበላይነት የተሰጠውን ትርጉም እናያለን፡፡

ዊሊያም የህግ በላይነትን አጭር እና ግልፅ በሆነ አገላለፅ እንደሚከተለው ይተረጉመዋል፤

“የህግ የበላይነት ማለት የመንግሥት አካላት፣ ባለስልጣናት(ሰራተኛውን ጭምሮ) እና ዜጎች በሕግ ጥላ ስር ሲወሰኑና ሲያከብሩ ነው“ የሚል ነው፡፡በአንድ ማህበረሰብ የመንግሥት ባለስልጣናትና ዜጎች የእለት- ተለት ስራቸውን የሚፈፅሙት በህግ ጥላ ስር ሆነው ህግን በማክበር ከሆነ በህግ የበላይነት የሚመራ ማህበረሰብ ይባላል፡፡ በዚህ ትርጉም ውስጥ የተገለፀው ህግ ለውጥን ሊያስተናግድ በሚችል መልኩ በጠቅላላ አገላለፅ የተረቀቀና በቀላሉ የሚረዱት፣ ተደራሽ የሆነ፣ ሊፈፀም የሚችል፣ ሁሉም በህግ ፊት እኩል የሆነበት እንዲሁም ህጉ በማይከበርበት ወቅት የማስፈፀሚያ ሥርዓትና ተቋማት ሊኖረው ይገባል፡፡ እነዚህ ሁኔታዎች ካልተሟሉ የሕግ የበላይነት ሊኖር አይችልም ይላል ዊሊያም፡፡

**ለምሳሌ ህጉን የማስፈፀሚያ ሥርዓት እና ተቋማት ከሌሉ ወይም ስራቸውን በአግባቡ ካልተወጡ የህግ የበላይነት እንደሌለ ይቆጠራል**

ለምሳሌ ህጉን የማስፈፀሚያ ሥርዓት እና ተቋማት ከሌሉ ወይም ስራቸውን በአግባቡ ካልተወጡ የህግ የበላይነት እንደሌለ ይቆጠራል። ባለስልጣኑም ሆነ ዜጋው ልጓም እንደሌለው ፈረስ እንዳሻው ይሰግራል ማለት ነው፡፡በሌላ በኩል ደግሞ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዊሊያም ከሰጠው ትርጉም በሰፋ መልኩ እንደሚከተለው ይተረጉመዋል። “የህግ የበላይነት የአስተዳደር መርህ ሲሆን ሁሉም ሰው፣ የመንግሥትም ሆነ የግል ተቋማት በግልፅ በፀደቀ፣ ያለአድሎ በእኩል በሚፈፀም፣ በገለልተኛ ፍርድ ቤት በሚተረጎም እና ከዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች የቃል ኪዳን ሰነዶች ጋር በተጣጣመ ህግ ተጠያቂ መሆንን የሚያመለክት ሲሆን ተጠያቂነትን፣ ርትዕን፣ ተገማችነትን፣ የስልጣን ክፍፍልን፣ በውሳኔ ሰጪነት ተሳታፊነትን፣ የዘፈቀደ አሰራርን ለማስወገድ እና የህግና የሥነ ሥርዓት ግልፀኝነትን ለማረጋገጥ የሚደረገውን ሂደትና ጥረት ይጨምራል” በማለት።

ፅንሰ ሃሳቡን የሚያጠኑ የህግ ሊቃውንት ከላይ ከተመለከቱት ትርጉሞች አንፃር እይታቸው በሁለት የሚከፈል ሲሆን ሕጋዊነትን መሰረት ያደረገ ዝቀተኛው (formal or procedural conception) እይታ እና መሰረታዊ ፍሬ ነገሮችን ያካተተ (substantive conception) የህግ የበላይነት በሚል ይከፈላል፡፡ ህጋዊነትን መሰረት ያደረገው ዝቅተኛው የህግ የበላይነት እይታ ዊሊያም ከሰጠው ትርጉም ጋር ተመሳሳይ ሲሆን ህግ መሰረታዊ የአስተዳደር መሳሪያ ሲሆን አግባብ ባለው ባለስልጣን ይመነጫል፣ ግልፅ፣ ተደራሽ፣ ተገማች፣ የረጋ እና ወደ ፊት የሚፈፀም መሆን እንደሚገባው ይገልፃሉ። መሰረታዊ

ወደ ገጽ 11 የዞረ

ዜና

# «ሀገራዊ ምክክሩ የሀገራችንን የወደፊት ዕጣ ፈንታ ስለሚወስን በንቃት ልንሳተፍበት ይገባል»

\- ምሁራን

**መዓዛ ማሞ**

አዲስ አበባ፡- ሀገራዊ ምክክሩ የሀገራችንን የወደፊት ዕጣ ፈንታ የምንወስንበት በመሆኑ ለስኬታማነቱ መረባረብ ይገባናል ሲሉ ምሁራን ተናገሩ።

በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ የትምህርትና ምርምር ምክትል ኃላፊ ሴና ዱጋሳ (ዶ/ር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ሀገራዊ ምክክሩ እንደ ሀገር ትልቅ ተስፋ የተደረገበት ጉዳይ ነው። ሀገራዊ ምክክሩ የሀገር ጉዳይ በመሆኑ ለስኬታማነቱ ምሁራን መሥራት ይጠበቅብናል።

ምሁራን በሚሠሩበት ቦታ፣ በመኖሪያ አካባቢያቸውና ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ የምክክሩን አስፈላጊነት እና ጠቃሚነት ለኅብረተሰቡ ማስገንዘብ እንዳለባቸው ጠቁመው፤ ሀገራዊ ምክክሩ የሀገራችንን የወደፊት ዕጣ ፈንታ የምንወስንበት በመሆኑ ምሁራን ምክክሩ እንዲሳካ በሚዘጋጁ መድረኮች ላይ ግንባር ቀደም ተሳታፊ በመሆን የሚጠበቅባቸውን ሚና ሊጫወቱ ይገባል ብለዋል።

ምክክሩ ለሀገራዊ ሰላም ትልቅ ፋይዳ ስላለው በተባለው ጊዜ እንዲደረግም ሁሉም የበኩሉን ሊወጣ እንደሚገባም ገልጸዋል።

የአወልያ ኮሌጅ ኃላፊ የሆኑት አቶ ሰይድ አስማረ በበኩላቸው ሀገራዊ ምክክሩ የሀገር ጉዳይ በመሆኑ ምሁራን በጉዳዩ ዋነኛ ተሳታፊ መሆን አለባቸው። ለምክክሩ በተከታታይ በሚደረጉ መድረኮች በንቃት በመሳተፍ ሀገራችን ካለችበት ችግር እንድትወጣ እና ሰላም እንዲፈጠር ምሁራን ኃላፊነታችንን መወጣት



ሴና ዱጋሳ(ዶ/ር)

ይገባናል ብለዋል።

ኮሚሽኑ ለምሁራን ማኅበረሰቡ ትልቅ አክብሮት እንዳለው ያስታወሱት አቶ ሰይድ፤ ሰላማዊ በሆነ መንገድ ችግሮች እና አለመግባባቶች እንዲፈቱ ሕዝቡን ግንባር ቀደም ሆኖ በማስተባበር ምሁራን ትልቅ ሥራ መሥራት እንዳለባቸው ጠቁመዋል። የሚደረገው ሀገራዊ ምክክር ጥሩ ውጤት እንዲያስገኝ ሁሉን ወገን አሳታፊ መሆን እንዳለበትም ገልጸዋል።

ሌላኛው አስተያየታቸውን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የሰጡት የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሕዝብ ግንኙነትና



አቶ ሰይድ አስማረ

ስትራቴጂክ ኮሚኒኬሽን መምህርና ተመራማሪ ሎሬት አማኑኤል አብዲሳ ምሁራን በየዘርፋቸው ለምክክሩ ምን ማበርከት እንዳለባቸው አስበው መንቀሳቀስ እንደሚጠበቅባቸው ተናግረዋል።

ምሁራን ከኋላ ብዙ ተማሪዎች እና ተከታዮች እንዳሏቸው የተናገሩት ምሁሩ፤ ምክክሩ ሀገራዊ አንድነትንና ሰላምን ለማምጣት የሚያስችል በመሆኑ ለዚህ ትልቅ ሀገራዊ ጉዳይ ምሁራን ትልቅ ሚና መጫወት አለባቸው ብለዋል።

ሀገራዊ ምክክር ስኬታማ እንዲሆን የኮሙኒኬሽንና



ሎሬት አማኑኤል አብዲሳ

ሚዲያ ሚና ከፍተኛ መሆኑን የሌሎች ሀገራት ተሞክሮዎች እንደሚያሳዩ ተናግረው፣ እሳቸው ባላቸው የኮሙኒኬሽን እውቀት ሂደቱን እንደሚያግዙ ተናግረዋል።

ምሁራን በጥናታቸው፣ በማስተማር ተግባራቸው እና በማማከር ሥራዎቻቸው ሁሉ ስለምክክሩ ግንዛቤ በመፍጠር እና በማስተባበር አስተዋጽኦ ማድረግ እንደሚጠበቅባቸውም ተናግረዋል። ለሀገራዊ ምክክሩ ስኬት በቀናነት እና በሀቀኝነት መሥራት ከተቻለ የሚፈለገውን ውጤት ማምጣት እንደሚቻልም አመልክተዋል።

## «የአመራር መተካካቱ ብልጽግና...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

አስታውሰው፤ ባላቸው አቅም ሁሉ ሀገራችንንና ፓርቲያችንን ለማገልገል ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል። ዛሬ ደግሞ በክብር መሸኘታቸው ብልጽግና 'በአብዮት' ሳይሆን በሪፎርም እንደሚያምን ትልቅ ምልክት ይሆናል ብለዋል።

አቶ ደመቀ ባለፉት ዓመታት ብልጽግናን በከፍተኛ ኃላፊነት ሲመሩ ቆይተዋል ያሉት ዐቢይ (ዶ/ር)፤ የብልጽግና መሥራችና መሪ እንደመሆናቸው ብልጽግና እስካለ ድረስ ስምና ታሪካቸው የሚቀጥል ይሆናል። የክብር ሽኝቱም ለዓመታት ተመካክረንበትና ተወያይተንበት የተደረገና ከምንም ጉዳይ ጋር የማይያያዝ መሆኑንም ጠቁመዋል።

የብልጽግና ፓርቲ ምክትል ፕሬዚዳንት አቶ አደም ፋራህ በበኩላቸው፤ የብልጽግና ፓርቲ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ጥር 13 እና 14 ቀን 2016 ዓ.ም ባካሄደው ስብሰባ ከተወያየባቸው ጉዳዮች መካከል የአቶ ደመቀ መኮንን የክብር ሽኝት ይገኝበታል።

አቶ ደመቀ መኮንን ለ32 ዓመታት በፌዴራልና በክልል በተለያዩ ኃላፊነቶች ያገለገሉ መሆናቸውን አስታውሰው፤ ለለውጡ እውን መሆንና ሀገራችን ለመጀመሪያ ጊዜ ላደረገችው ሰላማዊ የሥልጣን ሽግግር ስኬት ያበረከቱ መሆናቸውን ጠቅሰዋል።

በተጨማሪም ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው አቶ ደመቀ መኮንን እስካሁን ለሀገር፣ ለሕዝብና ለፓርቲያችን ለሰጡት አገልግሎትና ላበረከቱት አስተዋጽኦ ክብርና ምስጋና የሚገባቸው መሆኑን በመግለጽ፤ በክብር እንዲሸኙ የውሳኔ ሃሳቡን ለማዕከላዊ ኮሚቴው ማቅረቡን ገልጸዋል።

ጥያቄያቸው ተቀባይነት አግኝቶ በክብር የተሸኙት አቶ ደመቀ መኮንን እንዳሉት ደግሞ፤ 32 ዓመታት የአመራር ጉዞ በጣም ብዙ ስኬቶችና ፈተናዎችን ያየሁበት ነው። ብዙ ጉዳዮችን እንዳውቅም ያደረገኝ ዘመን ነው።

ከጊዜ ወደ ጊዜ የአመራርነትን ዋጋና የኃላፊነትን ሚዛን እየተገነዘብኩ እንድሄድ አድርጎኛል ብለዋል።

አሁን ላይ ጥያቄዬ በዚህ ክብርና በዚህ እውቅና ተቀባይነት በማግኘቱ ደስተኛም፤ ዕድለኛም ነኝ ያሉት አቶ ደመቀ፤ ምክትልፕሬዚዳንት ሆነው ለተመረጡት አቶ ተመስገን ጥሩነህ መልካም ምኞታቸውን ገልጸዋል።

ወደላይ ካለ አመራር ጋር ተከባብሮና ተጠሪነትን አክብሮ መምራት፣ ወደታች ያለን አመራርና ባልደረባ ማድመጥ፣ ኃይል ማሰባሰብና ማብቃት እንደሚያስፈልግ ጠቅሰዋል።

የብልጽና ፓርቲ ምክትል ፕሬዚዳንትነቱን ከአቶ ደመቀ መኮንን የተረከቡት አቶ ተመስገን ጥሩነህ፤ በተለያየ የኃላፊነት ቦታዎች ላይ ሳሉ ከፓርቲው ከፍተኛ አመራሮች ለተደረገላቸው ድጋፍ ምስጋና አቅርበዋል።

አቶ ደመቀ ባለፉት ዓመታት ያካበቱትን ልምድና ሀገራቸውን ለማገልገል የወሰዱት ቁርጠኝነት ሁላችንም ልምድ የምንወስድበት ነውም ብለዋል።

የብልጽግና ማዕከላዊ ኮሚቴ አቶ ደመቀ መኮንንን ከኃላፊነታቸው በክብር በመሸኘት አቶ ተመስገን ጥሩነህን ምክትል ፕሬዚዳንት አድርጎ መርጧል።

የብልጽግና ማዕከላዊ ኮሚቴ የፓርቲውን የአመራር የመተካካት መርህን እና የአሠራር ሥርዓት በመከተል ከትናንት በስቲያ ባካሄደው ማጠቃለያ ስብሰባ፤ በሙሉ ድምፅ አቶ ደመቀ መኮንን በክብር ሸኝቷል።

እንደ ኢቢሲ ዘገባ፤ በምትካቸውም የፓርቲው ሥራ አስፈጻሚ የነበሩትን አቶ ተመስገን ጥሩነህን ምክትል ፕሬዚዳንት አድርጎ በአብላጫ ድምጽ መርጧል።

## በክልሉ ከሀገር ውስጥ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ውስጥ ይንቀሳቀሳል ተብሎ ታቅዶ 800 ሚሊዮን ብር ኢኮኖሚው ውስጥ ተንቀሳቅሷል። ከ769ሺ በላይ ጎብኚዎች ክልሉን መጎብኘታቸውም ተጠቁሟል።

ቱሪስቶች ክልሉን ሲጎበኙ ትልቅ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ እንዳለው ተናግረው፤ ቱሪስቶቹ መጥተው ከሚከፍሉት የአገልግሎት ክፍያ ጀምሮ በተለያየ መልኩ የአገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ገንዘብ እንደሚያገኙም አመልክተዋል።

በመንፈቅ ዓመቱ 871 የውጭ ሀገር ቱሪስቶች ክልሉን ይጎበኛሉ ተብሎ ታቅዶ እንደነበረ አስታውሰው፤ ሁለት ሺህ 176 ጎብኚዎች ክልሉን መጎብኘታቸውን ተናግረዋል። በመንፈቅ ዓመቱ ከውጭ ሀገር ጎብኚዎች ከ215ሺ ዶላር በላይ ገቢ መገኘቱንም ተናግረዋል።

የገበታ ለሀገር ኮይሻ ፕሮጀክት አካል የሆነው የሀላላ ኬላ ሎጅ ሥራ ከጀመረ በኋላ ከፍተኛ የቱሪስት ቁጥር ወደ ክልሉ መምጣት ጀምሯል የሚሉት አቶ ፋንታሁን፤ ሁለተኛው የገበታ ለሀገር ኮይሻ ፕሮጀክት አካል የሆነው የጨበራ ዝሆን ዳና ሎጅም ተመርቆ ሥራ ከጀመረ በኋላ የክልሉ የቱሪዝም እንቅስቃሴ በከፍተኛ ሁኔታ መጨመሩን ተናግረዋል።

የሀላላ ኬላ ሎጅን በርካታ ቁጥር ያላቸው ቱሪስቶች እየጎበኙት እንደሆነ ተናግረው፤ የቱሪስቶቹ የቆይታ ጊዜም መጨመሩን ተናግረዋል።

የገበታ ለሀገር የኮይሻ አካል የሆነው የጨበራ ዝሆን ዳና ሎጅ ሥራ መጀመሩ እና የገበታ ለትውልድ አካል የሆነው በሚዛን አማን ከተማ የሚገኘው የደምቢ ሰው ሠራሽ ሐይቅ ላይ እየተሠሩ ባሉ የመስህብ ሥራዎች ከፍተኛ የማስተዋወቅ ሥራ መሠራቱ በክልሉ የቱሪስት እንቅስቃሴ እንዲጨምር ማድረጉን ተናግረዋል።

የጨበራ ዝሆን ዳና ሎጅ ለአገልግሎት ክፍት ከተደረገ በኋላ ጎብኚዎች ሎጁን ለመጎብኘት ከፍተኛ ፍላጎት እያሳዩ መሆናቸውን አመልክተው፤ በዚህም በሚቀጥሉት ስድስት ወራት ክልሉን የሚጎበኙ ጎብኚዎች ቁጥር ሊጨምር እንደሚችል ማሳያ ነው ብለዋል።

የቱሪዝም ዘርፉ ባለፉት ጊዜያት ትኩረት ተነፍጎት የቆየ ዘርፍ መሆኑን የተናገሩት አቶ ፋንታሁ፤ አሁን መንግሥት ለዘርፉ ከፍተኛ ትኩረት በመስጠቱ የሀገሪቱን ኢኮኖሚ እያነቃቃና የሀገር ገጽታ እየገነባ መሆኑን ተናግረዋል።

ክልሉን ለመጎብኘት የሚመጡ እንግዶችን ክልሉ በክብር እንደሚቀበል ገልጸው፤ የውጭና የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ወደ ክልሉ በመምጣት ክልሉን እንዲጎበኙ እንዲሁም በዘርፉ እንዲያለሙ ጥሪ አቅርበዋል።

## ኢትዮጵያ በዲፕሎማሲው መስክ ቀዳሚና ተደማጭ እንድትሆን...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

መመሪያ መስጠቱን ጠቁመዋል።

አምባሳደሮቹ ከሚመሯቸው የሚሲዮን ሠራተኞችና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር የቅርብ ግንኙነትና ጥብቅ ትስስር መፍጠር እንዳለባቸው በማጠቃለያው መነሳቱን አስታውቀው፤ ለዚሁ የሚያግዝ ትክክለኛ ዕቅድ በማዘጋጀትና ይህንኑ መሠረት አድርጎ መንቀሳቀስ እንደሚጠበቅባቸው መገለጹን አስረድተዋል።

የኢትዮጵያ የዲፕሎማሲ እንቅስቃሴ ግብ የሀገሪቱን ተደራሽነት፣ ተደማጭነትና ተፈላጊነት የሚጨምር ሊሆን ይገባል ያሉት አምባሳደር መለስ፤ ኢትዮጵያን የወከሉ አምባሳደሮች ሀገሪቱ ቀዳሚና ተደማጭ የምትሆንበትን ተግባር ሊያከናውኑ ይገባል ብለዋል።

ቃል አቀባዩ እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ ከጎረቤት ሀገራትና ከሌሎች ሀገራት ጋር ያላትን የሁለትዮሽ ግንኙነት የበለጠ ለማጠናከርና አዳዲስ ግንኙነቶችንም ለመፍጠር ሚሲዮኖች የበለጠ ሊሠሩ እንደሚገባ በስብሰባው ተመላክቷል።

ከሁለትዮሽ ግንኙነት በተጨማሪም በባለብዙ ወገን የዲፕሎማሲ ሥራዎች ሀገሪቱ ንቁ ተሳታፊ ሆና እንድትቀጥል ማድረግ ይገባል ሲሉ አቶ ደመቀ መናገራቸውን ጠቅሰው ቃል አቀባዩ ጠቁመዋል።

የዲፕሎማሲ እንቅስቃሴው ግንባር ቀደምና ለሚመለከተው አካል ቀድሞ የሚደርስ መሆን እንዳለበት በስብሰባው ትኩረት ተደርጓል ያሉት ቃል አቀባዩ፤ አምባሳደሮች ኢትዮጵያን በዓለም አቀፍ መድረኮች ከመወከል ባለፈ የዲፕሎማሲው ዘርፍ ጎልቶ እንዲወጣ ማድረግ እንዳለባቸው አጽንኦት ተሰጥቷል ብለዋል።

ኢትዮጵያ ከተለያዩ ሀገራት ጋር ያላት ግንኙነት የጋራ ተጠቃሚነት፣ መከባበርንና የሁለትዮሽ ግንኙነትን እንዲሁም የባለብዙ ወገን የዲፕሎማሲ እንቅስቃሴን ባጠናከረ መንገድ መከናወን እንዳለበት በስብሰባው መመሪያ ተሰጥቷል ብለዋል።

በአጠቃላይ የዲፕሎማሲ ሥራው የሀገሪቱን ተደራሽነት፣ ተደማጭነትና ተፈላጊነት የሚጨምር ሊሆን እንደሚገባ አጽንኦት ተሰጥቷል ሲሉ ቃል አቀባዩ ተናግረዋል።

አምባሳደሮቹ እንደየተመደቡበት ሀገር ተጨባጭ ሁኔታ የኢትዮጵያን ገጽታ በመገንባት፣ ኢንቨስተሮችን በመሳብ፣ የተለያዩ የቱሪስት መዳረሻዎችን በማስተዋወቅ፣ ለኢትዮጵያ ምርቶች ተገቢውን ገበያ በማፈላለግ፣ የፋይናንስና የቴክኒክ ድጋፍ ሥራዎች ላይ በማተኮር ውጤት ማስመዝገብ እንዳለባቸው በስብሰባው አቅጣጫ መቀመጡን አስታውቀዋል።

ቃል አቀባዩ እንደገለጹት፤ ለሁለት ሳምንት በዘለቀው የሚሲዮን መሪዎች ስብሰባ የኢትዮጵያን የሁለትዮሽ ግንኙነት የበለጠ አጠናክሮ ለማስቀጠል የሚቻልባቸው ጉዳዮች ላይ ሰፊ ውይይት ተደርጓል።

በተጨማሪም በተለያዩ ሀገራት ተመድበው የሚሠሩ የሚሲዮችን መሪዎች በኢትዮጵያ የሚገኙ የተለያዩ የልማት ፕሮጀክቶችን የጎበኙ ሲሆን፤ ለፕሮጀክቶቹ ስኬት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ጥሪ መቅረቡን አምባሳደር መለስ አስታውቀዋል።

# ሃያ አንድ ዓመታት በምክር ቤት

ሰላማዊት ውቤ

የአንድ ሰው ስብዕናና ማንነቱ ከሚገነባባቸው መንገዶች አንዱ ቤተሰብና አስተዳደግ ቢሆንም አካባቢ ማህበረሰብና ትምህርት ቤት የየራሳቸውን ሚና ይጫወታሉ፡፡ ግለሰቡ ከልጅነቱ እስከ ወጣትነቱ በሚያሳልፈው ዕድገት በጊዜው ወይም በዘመኑ የነበረው መንፈስና አስተሳሰብ አስተዋፅኦ አለው፡፡

የዘመኑ አስተሳሰብ የወቅቱን ትውልድ ምርኮኛ ያደርገዋል፡፡ ይህ በብዙ ሀገሮች የነበረ፣ የታየና ያጋጠመ ክስተት ነው፡፡ በሀገራችን ኢትዮጵያም በንጉሡ ነገሥቱ ዘመን የነበረውን አስተዳደርና አገዛዝ በመቃወም በተለይ የተማረው ትውልድ ግንባር ቀደም ነበር። እ.ኤ.አ. በ1960ዎቹ አጋማሽና 1970ዎቹ መጀመሪያ በዓለም ላይ የነበረው የዘመኑ መንፈስ የኢትዮጵያንም ወጣቶች ሸውታው ነክቷቸዋል፡፡ በጊዜው ከነበሩት ወጣቶች አንዱ የሆኑት አቶ ተሾመ እሸቱ ከሸውታው አላመለጡም፡፡ በሥርዓት ላይ ካመፀው ትውልድ ጋር አምጸዋል፤በኢህአዴግ ዘመንም በአራት ምርጫዎች በመሳተፍ ለ21 ዓመታት በምክር ቤት ቆይተዋል። በርካታ የሕይወት ተሞክሮ ያላቸው እኒሁ ግለሰብ የዛሬው የህይወት ገጽታ እንግዳችን ናቸው፡፡

### ልጅነት፣ አስተዳደግና ትምህርት

ትውልዳቸው ጎንደር ጠቅላይ ግዛት፣ ሰሜን አውራጃ ሲሆን፤ አውራጃው በስተምዕራብ በኩል ከዳባት ጋር ወሰንተኛ ነው፡፡ ከተከዜ ወንዝ ጋር ግጥም በሆነው በዚህ አውራጃ በ1942 ዓ.ም ለእናታቸው የመጀመሪያ፣ ለአባታቸው ደግሞ አራተኛ ልጅ የሆኑት አቶ ተሾመ እሸቱ ተወለዱ። በወቅቱ ትምህርት ብርቅ ስለነበር እድሉን የሚያገኙትም የአስተዳዳሪና የሹም፣ የፖሊስ አዛዦች ልጆች ብቻ ነበሩ፡፡ በቤተሰብም ጭምር ድጋፍ አግኝተው ትምህርት ቤት የሚሄዱት፤ የሚፈቀድላቸውም እነሱ ብቻ ናቸው፡፡ በሀገሬው በተለይም በገበሬው ዘንድ ትምህርት ብዙ ቁብ አይሰጠውም ነበር።

ይሁንና "ሹም" በሚባሉት ሰዎች፤እንዲሁም በሕዝቡ ዘንድ "አደባባይ መዋል" የሚባል ነገር አለና ልጆቻቸው "የአደባባይ ሰው" እንዲሆኑ ስለሚሹ እንዲማሩ ያደርጉ ነበር። አቶ ተሾመም አያታቸው የአደባባይ ሰው ስለነበሩ እንዲማሩ ግፊት ያደርጉባቸው ነበር። እርግጥ የአማርኛ ትምህርት በተወሰነ ደረጃ እሳቸውና እኩዮቻቸው ይማሩ ነበር። እሳቸው ግን በተለይ ንባብን በተመለከተ ጥሩ ጀርባ ነበረኝ ይላሉ። የቤተክህነትን ትምህርት እንደ "አንቀፀ ብርሃን"፣ "ውዳሴ ማርያምን"፤"ዳዊት መድገም"ን ጨምሮ በመጠኑ ተከታትለዋል። እነዚህን አጥርተው በመዝለቃቸው ለሚቀጥለው የትምህርት ዘመናቸው እምብዛም እንዳልተቸገሩም ነው የሚያስረዱት።

ከዚህ ሁሉ በኋላ ደግሞ ጎንደር ከተማ ላይ ትምህርታቸውን ሲጀምሩ ቀና ሆነላቸው፣ በወቅቱም እሳቸው ተወልደው ካደጉበት ወረዳ ጎንደር ድረስ መጥተው ትምህርት ቤት የገቡት አራት ልጆች ብቻ ነበሩ። ዘመኑም 1950 ዓ.ም ። የእሳቸው ቤተሰብ ግን የአደባባይ ሰው እንዲሆኑ ይገፋፏቸው ስለነበር ትምህርታቸውን ወደፊት ለመግፋት ስንቅ እንደሆናቸው ያምናሉ፡፡ በ1964 ዓ.ም የ8ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና (ሚኒስትሪን) ተፈተኑ። ፈተናውንም በማለፋቸው እዛው ጎንደር ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ቀጠሉ። በ1966 ዓ.ም ግን አብዮቱ በመፈንዳቱ ትምህርት ተቋረጠ። በመካከል ለተወሰነ ጊዜ ትምህርት ቤቶች ተከፍተው ትምህርት ተጀምሮ የነበረ ቢሆንም በ1967 ዓ.ም "የዕድገት በሕብረት የዕውቀትና የሥራ ዘመቻ" በመታወጁ እንደገና ተዘጋ።

"....እርግጥ ዘመቻው እኔን አይመለከትም ከአስራ አንደኛ ክፍል ጀምሮ እስከ ከፍተኛ ተቋማት የነበሩት ናቸው እንዲዘምቱ የተደረገው።ይሁንና ዘመቻው እክል ስለገጠመው ተቋረጠ። የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች የነበሩት እንዲዘምቱ እና ለዚህም ዝግጅት እንዲያደርጉ ሲነገራቸው እኔም ዝግጅት አደረግኩ። በዘመቻው ብዙም ሳንገፋ ዘመቻው ተቋረጠ "ይላሉ፡፡

እንዲህ እንዲህ እያሉ አቶ ተሾመ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን አጠናቀው ከፍተኛ ትምህርት በመግባት የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን ለማግኘት ቻሉ።

አቶ እሸቱ ተምረው ዲግሪ ካገኙበት ሙያ ውጪም የሰላና ቶሎ የሚረዳ አእምሮ ስለተቸራቸው የትኛውም የሙያ ዘርፍ ላይ ያለ ሰው ስለአንድ ጉዳይ ሲናገር ቶሎ የሚረዱና የሚገባቸው ናቸው። ይህንንም በአንደበታቸው እንደሚከተለው ይገልጹታል፡፡

"......ለምሳሌ ኢኮኖሚስቶች ተሰብስበው ሲያወሩ፣ ሲወያዩ፣ የእነሱን ያህል ውስጡ ዘልቄ መተንተን ቢያቅተኝም በደንብ ይገባኛል። በተመሳሳይ ስለ አስተዳደር፣ ኢኮኖሚክስ ወዘተ ሲወሩም ያለችግር እረዳለሁ" በማለት ይናገራሉ።

### የፖሊቲካ ንቃትና ተሞክሮ

አቶ ተሾመ እሸቱ በልጅነታቸው ያዩት ለኋለኛው ሕይወታቸው መነሻና መሠረት ሆኗቸዋልም። አምባ ጊዮርጊስ ሲማሩ መውጪያና መውረጃያቸው በፍርድ ቤት በራፍ ነበርና ሁሌም የሚመለከቷቸው ትዕይንቶች ይስቧቸዋል። ከፍርድ ቤቱ በራፍ ላይ በተቸከለ እንጨት ላይ ታስረው መሬቱን እየጎደፈሩ የሚውሉ ፈረሶችን ያስተውላሉ። ከዚያም በላይ አርሶ አደሩ ሥራ ፈትቶ የመጣበት ጉዳይ ሳያልቅ ፋይሉ ወደ ወረዳው ተመልሶ ባለጉዳዮቹ ወደ ቤታቸው ሲመለሱ ያለውንም ስሜት ይረዳሉ ።

ሌላው እያዩ ያደጉት ደግሞ አስተዳዳሪዎች ከትንሿ ዶሮ ጀምሮ የገበሬውን ፍየሉን ሲያርዱበት ነው። ይህ በአይናቸው ያዩትና የሚሰጠውንም ፍርድ እየሰሙ የኖሩበት ነው። አብዛኛው የክሱ ይዘት፣በተከሳሽና በከሳሽ መካከል ያለው ውዝግብ ሲጠቃለል "እወለዳለሁ አትወለድም" የሚል ነው። በአካባቢው ከሞላ ጎደል ክስ የሚከፈተው መሬትን በውርስ ለማግኘት ሲሆን፤ በድንበርና ከእርሻ ሁኔታ ጋር በተያያዘ ነበር። በተለይ ከሚያስታውሱት የምስክር አቀራረብ አንዱ ችግር ሲሆን፤ ይህም ለአብነት ሊጠቀስ የሚችል ነው። በአንድ የአዝመራ ወቅት ወደ ዘመናዊ ትምህርት ቤት ከመግባታቸው በፊት ያዩትን ያስታውሳሉ።

አንድ የአባታቸው የቅርብ ዘመድ የሆኑ ሰው ቤተሰባቸው ሁሉ በወባ ታሞ እቤት ውለዋል። በሕመሙ ወቅት ያልተኙት እሳቸውና አንዲት ሠራተኛቸው ብቻ ነበረች።አውድማ ላይ የአተር ክምር ነበር።ጭላዳ ዝንጀሮ ክምሩን እያፈረሰ ሲያስቸግራቸው ልጅቱን ይዘው በመውጣት አተሩን ይወቃሉ።በዚህን ሰዓት ነበር ከምክትል ወረዳ ገዢ በታች የነበሩ አጥቢያ ዳኞች የመጡት። ተሾመ ለምን እንደመጡ እንኳን አያውቁም። ብቻ ሰዎቹ በዚያ ሲያልፉ ያቺን ሴት ልጅ ያዩዋታል። በሬዎቹን አውድማ ላይ እያዞረች ነበር።

አጥቢያ ዳኞቹም "ለምን አውድማ ላይ አስገባሃት?" ብለው የክስ መሰል ጥያቄ አቀረቡላቸው። እሚገርመው "ጉልበት በዝብዘሃል፣ አላቅሟ አሠርተሃታል" አልነበረም ጉዳዩ።"ባህል ጥሰሻል" ነበር። እንግዲህ ባህሉ "ሴት ልጅ አውድማ አትገባም" ነበር የሚለው ኋላ ተሾመ እንደገባቸው። ምክንያቱ ደግሞ በባሕል የነበረውና በጊዜውም ሕግ ሊያስጥብቀው የሚሻው ነገር "ሴት ልጅ አውድማ ከገባች እህል አይበረክትም" የሚል ነበር።

በዚሁ እና መሰል ምክንያቶች እነ መንግሥቱ ኃይለማርያም ንጉሡን ማውረዳቸው ትክክል ነው ብለው ያምናሉ። ይሁንና ያን ሁሉ ወጣት መግደላቸው ግን ትክክል አልነበረም ይላሉ። ይንንም በረሃ የመግባታቸው ምክንያት አድርገው ይወስዱታል አቶ ተሾመ፡፡ አንድም ቀን ጠመንጃ ተሸክመው በረሃ እውላለሁ ብለው አስበው እንደማያውቁ ይናገራሉ። እሳቸው ያው የአደባባይ ሰው እሆናለሁ ብለው ነበር የሚመኙት።ይሄው ዛሬ ከድሃው ከሀብታሙ ጋር እንዲኖሩ ያደረጋቸው ያ ተሞክሯቸው እንደሆነ በኩራት ያስታውሳሉ፡፡

በ1966 ዓ.ም ዐመፅ ሲጀመር እሳቸው አምባ ጊዮርጊስ ሰላማዊ ሰልፍ እየመሩ ነበር። በዛን ጊዜ ነበር አውራጃ ገዢው የመጡት።ተሾመ ቀደም ቀደም እያሉ በነበረበት ሰዓት አብረዋቸው የነበሩት የአካባቢው ሰዎች "አንተ ዝም በል፤ ለሱ እኛ እንበቃዋለን" ብለው አከላከሉዋቸው። እሳቸውም እንደተነገራቸው አፋቸውን ከርክም አርገው ዝም አሉ። አውራጃ ገዢውም ንግግራቸውን በሰፊው ጀመሩ።

የመልዕክታቸው አብዛኛው ክፍል በጠላት ዘመን ስለሰሯቸው ተግባራት፣ ጀብዱዎች ወዘተ የሚያትት ነበር። ይሁንና አርሶ አደሩ የጠየቀው "አትንኩን" የሚለውን አጭር



ጥያቄ እንጂ የኢጣሊያን ዘመን ታሪክ እንዲተረክለት አልነበረም። እንግዲህ እሳቸው ንግግራቸውን እንዳበቁ በሚገርም ሁኔታ ከተሰብሳቢው መሃል በጣም አጭርና ያን ሁሉ ንግግራቸውን የሚያኮስምን ምላሽ ተሰጠ።"ቢትወደድ የት ሄዱ?" የሚል ጥያቄ ተነሳ፡ ፡ መልዕክት አስተላላፊውም "ሁመራ እርሻ"፣ ብለው መለሱ፡፡ ተሰብሳቢውም አስተዳዳሪውም እርሻ፣እኛም እርሻ፣ ታዲያ መች ነው እኛን በቅጡ የሚያስተዳደሩት? የሚል ጥያቄ ቀረበላቸው።

መልዕክተኛው ግን መልስ አልበራቸውም። ተሰብሳቢው ቢሰለቸውም "የኛ በቅሎዎች ተሠርቀው የሚገቡት እርስዎ ዘመዶች ቤት ነው"፤ እኛ በቅሎቻችንን ጠብቁልን ስንል እሳቸው ደግሞ ስለጠላት ዘመን ያወራሉ በማለት ሰዉ አማረረ።

በአጠቃላይ በአጼው ዘመን ገበሬው የበይ ተመልካች ነበር፡፡ ያመረተውን ምርት በገፍ ከመውሰድ ውጪ ብሶቱን እንኳን የሚያዳምጠው አልነበረም፡፡ይህ ሁኔታ አማሮኝ ነበር እንደ አብዛኛው ወጣት ኢህአፓ የሚባለውን ፓርቲ የተቀላቀልኩት ይላሉ። በጊዜው የነበረው ቅስቀሳ የወቅቱን አስተዳደር ለመታገል የሚል ስለነበር እኔም በተሞክሮ ያየሁትና የማውቀው ሥርዓት

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ

# ሃያ አንድ ዓመታት...

ከ6ኛ ገጽ የዞረ

ስለነበር አምኜ ተቀላቀልኩ፡፡

ስለሀገር ማውራት፣ ማንበብ፣ መከራከር፣ ስለሕዝብ ጉዳይ ማውራትና የመሳሰሉትን ያስተማራቸው ድርጅታቸው እንደሆነም ነው የሚናገሩት።

**የወረዳና ዞን አስተዳዳሪነት**

አቶ ተሾመ ኢህአፓን ተቀላቅለው አጼውን ለመጣል በሚደረገው ትግል ውስጥ ንቁ ተሳታፊ ነበሩ። በዚህም የፖለቲካ አስተሳሰባቸውን አዳበሩ፤ከህዝብ መቆም ባህርያቸው አደረጉ፡፡ይህ አስተሳሰባቸው እየጎለበተ ሄዶ ኢህአዴግ ከገባ በኋላ በምርጫ ተወዳደሩ፡፡ የጎዛምንን ወረዳ ወክለው ተወዳድረው አሸነፉ፡፡

የጎዛመን ወረዳን አስመልክተው ለሳቸው በሥፍራው ለመመረጥም ሆነ 500 ሰው ማስፈረም አስቸግሯቸው አያውቅም። ከወረዳ አስተዳዳሪ ጀምሮ እስከዞን አስተዳዳሪነት የደረሱበት ተሞክሮና ልምድ አላቸው።

በጎዛመን ቆይታቸው የተሠሩት ስራዎች ብዙ ነበሩ ይላሉ። እሳቸው ከመመረጣቸው በፊት የጎዛምን ወረዳ በመንገድ እጥረት ትሰቃይ ነበር፡፡ እርሳቸው የወረዳ ብሎም የዞን አስተዳዳሪ ከሆኑ በኋላ ደረጃ በደረጀ የሕዝቡን ጥያቄ አቅም በፈቀደ መጠን ለመመለስ ጥረት አድርገዋል፡፡በጎዛምን ወረዳ መንገድ በመስፋፋቱ አንድም ቀበሌ መኪና እማይገባበት የለም። ማዳበሪያ በትልቅ መኪና መጥቶ ነው የሚራገፈው።የገበሬ እህል በመኪና ተጭኖ ነው የሚወጣው።ለምሳሌ እሳቸው ዞን አስተዳዳሪ ሆነው ሥራ የጀመሩት በ1986 ዓ.ም. አካባቢ ነበር። በዚህ ወቅት ምሥራቅ ጎጃም 80 ሺ ተማሪ ነበረው። በ1992 ዓ.ም ለቅቀው ሲወጡ ግን 280ሺ ተማሪ በትምህርት ገበታው ላይ ይገኝ ነበር። ቀን ከሌሊት ነበር የምንሠራው ይላሉ፤መጀመሪያ ለጥራት አልነበረም ሩጫቸው፤ ፍላጎታቸው ልጆች ትምህርት ቤት እንዲውሉ ነበርና ባሕር ዛፍ በመቁረጥ የተማሪ መቀመጫ እየሠሩ፣ በጭቃ ምርግ ክፍሎችና ቤቶችን እያዘጋጁ ነው ትምህርት ቤት ያቆሙት ።በሌላውም እንዲሁ ነበር አሠራራችን ይላሉ፡፡

በግብርናውም የእሳቸው 16 ወረዳዎች የሚወስዱት ማዳበሪያ ከ12ሺ. አይበልጥም ነበር። በ1983 ዓ.ም ወደ ወረዳዎች ሲገቡና በ1992 ሲወጡ 52 ኪሎ ግራም የነበረውን 59 ኪሎግራም ነበር የደረሰው። 7 ኪሎ ብቻ ነበር ጭማሪው።

አስተዳዳሪ ሆነው አንድም ቀን ፖሊስ አጅቧቸው አያውቅም። እዛው እያሉ ዞን አስተዳዳሪ ሆነዋል። የደበረማርቆስ ዞን አስተዳደሪነትን ከ1985 ዓ.ም.እስከ 1986ዓ.ም ለአንድ ዓመት ተኩል ያህል ሠርተዋል። በ1992፤በ1997፤በ2003እና በ2007 በተደረጉት ምርጫዎች በመሳተፍ አሸንፈዋል፡፡ በመጨረሻም 21 ዓመት ካገለገሉ በኋላ 2013 ዓ.ም ጡረታ ወጥተዋል፡፡

**የፓርላማ ቆይታ፣ ክርክርና ውይይት**

ፓርላማ እያሉ የገጠማቸውን አስመልክተውም ሲያስታውሱ የማስወረድ ሕግ ሲመጣ ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት ነበር የሠሩት፡፡ሕጉ ራሱ ሲመጣ ጀምሮ የፖለቲካ ፍላጎትና ስሜት ተጭኖት ስለነበርና ሰብዓዊ መብትን ምክንያት በማድረግ ነበር ጫና የተፈጠረው ይላሉ።

ያልተፈለገ እርግዝናን በመከላከል በኩል የሰብዓዊ መብት ተሟጋቾች ቢሠሩ፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ቢያስተምሩ፣ ያልተፈለገ እርግዝና ከተከሰተ በኋላ ግን የማስወረድ መብት ይኑር በሚል ብዙ ተሄዶበታል። ከብዙ እልህ አስጨራሽ ሙግትና ክርክር በኋላ ግን ሕግ ሆኖ ወጣ።ይህ የማስወረድ ሕግ ወደ ፓርላማ ሲመጣ የሕግና አስተዳደር ኮሚቴ ነበሩ እሳቸው። በመጨረሻ በተደረገው እልህ አስጨራሽ ጥረት ሕግ ሆኖ በመጨረሻ ወጣ፡፡

አቶ ተሾመ ሃያ አንድ ዓመት በምክር ቤት ሲቆዩ ወደ ስድስት በሚሆኑ ኮሚቴዎች ውስጥ አባልና አመራር በመሆን ሠርተዋል።



ከመጀመሪያው ጀምሮ ብዙ ዘመን ፓርላማ በመቆየታቸው ተሞክሯቸውን ለአዳዲሶቹ ተመራጮች ማካፈልም ተቀዳሚ ስራቸው ነው። የፓርላማውን ሁኔታም በማሳየትና በማስረዳት አስተዋፅዖ አበርክተዋል። እንደሳቸው አገላለፅ በፓርላማው ብዙ ዓይነት ክርክሮች ይደረጋሉ። ክርክር መልካም ቢሆንም ገንቢነቱ ላይ ትኩረት ከማድረግ ይልቅ ሰው ፍረጃ ወስጥ የሚገባበት አጋጣሚ ሰፊ መሆኑን ያስረዳሉ፡፡ ይህ ደግሞ ን ብዙ ዋጋ አስከፍሎናል ይላሉ፡፡ ከዚህ በኋላ ያለው የፓርላማ ሂደትም ከዚህ የጸዳ ቢሆን ግቡን ይመታል በማለት አቶ ተሾመ ከልምዳቸው በመነሳት አስተያየታቸውን ይስጣሉ።

በፓርላማ ቆይታቸው የገረማቸውንና በጣም ያሳዘናቸውን ገጠመኝ ሲገልጹም "....በ1996 ወይም 1997 ላይ አንድ ባለስልጣን ለኦዲት ተጠራና በመሥሪያ ቤቱ ውስጥ የሴቶች ተሳትፎ ምን እንደሚመስል ተጠየቀ። መልሱ፣- "የኔ መሥሪያ ቤት እኮ የሙያ መሥሪያ ቤት እንጂ የፖለቲካ መሥሪያ ቤት አይደለም" አለ። የኢህአዴግ የፖለቲካ ቢሮ ባልደረባ እና የምክር ቤት አባል ነው።

ሆኖም በፖለቲካ አስተሳሰብ የሴቶች ጉዳይ ዋነኛ የፖለቲካ ጉዳይ መሆን ሲገባው ይህን የመሰለ መልስ መስጠቱና ከገዢው ፓርቲም ጋር የጠበቀ ቁርኝት ስለነበረው ምንም አለመባሉ እስካሁን ያንገበግበኛል፡፡ብዙ ጊዜ የምንናገረውና በተግባር የምንፈጽመው ስለሚለያይ ይቆጨኝ ነበር» ሲሉ አቶ ተሾመ በምክር ቤት ቆይታቸው የታዘቡትን በጥቂቱ ይናገራሉ፡፡

ምክር ቤቶች የሀሳብ መንሸራሸርያ መድረኮች መሆን ይገባቸዋል፡፡የምክር ቤት አባላት ታማኝነታቸው ለህሊናቸውና ለመረጣቸው ህዝብ ነው፡፡ስለዚህም ሁልጊዜ ለህዝብ ጥቅም መቆም አለባቸው፡፡

አቶ ተሾመ እንደሚያምኑበት የምክር ቤት አባላት በምክር ቤት በሚቆዩበት ጊዜ ሁሉም ነገር አልጋ በአልጋ ላይሆንላቸው ይችላል፡፡የሚጎረብጣቸው ጉዳይም ሊከሰት ይችላል፡፡ሆኖም ለህዝብ ጥቅም የቆሙ ናቸውና የሚደርስባቸውን ፈተና በመጋፈጥ ከህዝብ ጎን መቆም እንደሚኖርባቸው ይናገራሉ፡፡

እርሳቸው በቆዩባቸው 21 አመታት ህሊናን የሚፈታተኑ፤በራስም ላይ አደጋ የሚያስከትሉ በርካታ ፈተናዎችን ተጋፍጠው እንዳለፉ ያስረዳሉ፡፡በተለይም ከገዢው ፓርቲ አስተሳብ ወጣ ያሉ ሃሳቦችን መስጠት ወይም በሌሎች አካላት የሚሰጡ አስተያየቶችም መደገፍ ዋጋ ያስከፍል ነበር፡፡ሆኖም ከህዝብ የሚበልጥ ጉዳይ የለምና በርካታ ተጽዕኖዎች ቢኖሩም ሁኔታዎችን እንደአመጣጣቸው እያለፉ 21 አመታትን በትግል መቆየታቸውን ይናገራሉ፡፡

በ21 ዓመታት የምክር ቤት ቆይታቸው ከታዘቧቸው ጉዳዮች መካለል ዋነኛው የምክር ቤት አባለት በህገመንግስቱ የተሰጣቸውን ኃላፊነት ለመወጣትና የህዝብን ጥያቄ ለማንጸባረቅ በሚያደርጓቸው ጥረቶች ሁሉ ከተለያዩ አካላት ዛቻዎችና ማስፈራርያዎች ይደርስባቸው እንደነበር ነው፡፡

አንዳንድ የፓርላማ አባላት ዛቻና ማስፈራሪያዎችን በመፍራት ከመናገር ቢቆጠቡም ሌሎች ደፋሮች የህዝብን ጥቅም በማስቀደም የመሰላቸውን ሃሳብ ከመሰንዘር ቦዝነው እንደማያውቁ ያስረዳሉ፡፡በተለይ አዳዲስ የፓርላማ አባላት በምርጫ አሸንፈው ምክር ቤት ሲገኙ ቀድመው የጠበቁትና ሆኖ የሚገኘው ስለሚለያይባቸው ቶሎ ተስፋ የሚቆርጡም እንደነበሩ ይናገራሉ፡፡

አንዳንድ ጊዜ ደግሞ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የውይይትና የምክክር ቦታ መሆን ሲገባው መሾም ፤መሸለም ለሚሹ ሰዎች የፖለቲካ ነጥብ ማስቆጠሪያ የሚሆንበት አጋጣሚ እንደሚኖር አቶ ተሾመ ይናገራሉ፡፡ ወቅታዊ የፖለቲካ ትኩሳቱን በማራገብ እና በእሰፈጻሚው አካል ዕይታ ውስጥ በመግባት ለመሾም የሚጥሩ በርካታ ሰዎች መኖራችውን ያስረዳሉ፡፡የእነሱን አስተሳሰብ መታገል በራሱ ፈተና ነው ይላሉ፡፡

በሌላም በኩል የምክር ቤት አባላት ህዝብ የወከላቸው እንደመሆኑ መጠን ለሰብአዊ መብቶች ጥሰት ተጠያቂነትን በማረጋገጥ፣ የሕግ በላይነትን በማስፈን፣ መንግሥትና የስራ አስፈጻሚ አካላቱ በመሉ ለሰብአዊ መብቶች መከበር፣ መጠበቅና መሟላት ያላቸውን ቁርጠኝነት እንዲያድሱና እንዲተገብሩ ልዩ ትኩረትና ክትትል ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

ሆኖም አንዳንድ ጊዜ ምክር ቤቱ አዋጆችን በማጽደቅ ይጠመድና አስፈጻሚውን ችላ ሲለው ይታያል፡፡ይህ ሲሆን ደግሞ መልካም አስተዳደር ይሰተጓጎላል፤ሌብነት ይንሰራፋል አልፎ ተርፎም ሰብአዊ መብት ጥሰት ይበረከታል፡፡

ስለሆን የተለያየዩ አዋጆችን ከማጽደቅ በላይ ሰው ነክ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ማተኮሩ የበለጠ ውጤታማ ያደርጋል። በየአካባቢው ያሉ የመልካም አስተዳድ ችግሮችን እየነቀሱ እንዲስተካከሉ ማድረግ የእያንዳንዱ ምክር ቤት አባል ኃላፊነት ነው፡፡ ከዚሁ ጎን ለጎን ደግሞ አጥፊዎች ላይ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ ማመላከትና ህዝብን የሚያንገላቱ አካላት ከቦታቸው እንዲነሱና እንዲጠየቁ ማድረግ የምክር ቤት አባላት ግዴታ ነው፡፡ነገር ግን በወቅታዊ ስራዎች በመጠመድ ህዝቡ የሚማረርባቸው ጉዳዮች ችላ ሲባሉ ይታያሉ፡፡

ሌላው እና ዋነናው ጉዳይ ሙስና ነው፡፡አንድ ሰው በምርጫ አሸንፎ ምክር ቤት ሲገባ ከተጣሉበት ኃላፊነቶች መካከል የሀገርና የህዝብን ሀብት መጠበቅ አንዱ ነው፡፡ አስፈጻሚው አካል ያገኘውን አጋጣሚ ተተቅሞ ሲዘርፍና የሀገርና የህዝብ ሃብት ሲያባክን የምክር ቤት አባላት ለምን ብለው መጠይቅ ይጠበቅባቸዋል፡፡አንዳንድ ጊዜ እኮ የሚሰርቁ ሰዎች ሲሾሙና ለበለጠ ኃላፊነት ሲታጩ እታዩ ዝም ተብለው ሲታለፉ ይታያል፡፡እነዚህ ሌቦች የበለጠ እንዲዘርፉና የሀገርና የህዝብ ሀብት እንዲየባክኑ እድል ሲሰጣቸው የምክር ቤት አባላት ታግለው ሹመታቸውን ማስቀረት ይጠበቅባቸዋል፡፡ግዴታቸውም ጭምር ነው፡፡

አቶ ተሾመ የምክር ቤት አባላት በነበሩባቸው አራት የምርጫ አመታት በተለያዩ ወቅቶች ከሕግ ውጪ የተፈጸሙ ግድያዎች፣ ከመጠን ያለፈ የኃይል አጠቃቀም፣ የዘፈቀደና ከፍርድ ወይም ክስ በፊት ያለ የተራዘመ እስር፣ በጋዜጠኞችና በፖለቲካ ተቃዋሚዎች ላይ ያነጣጠረ እስራት እና የአንዳንድ እስር ቦታዎች አያያዝ ሁኔታ አሳሳቢነት እየጨመረ በመምጣቱ የምክር ቤቱን ልዩ ትኩረት አግኝቶ ውይይት ሲካሄድባቸው እንደነበር አስታውሰዋል፡፡

በጦርነትና በግጭት እንዲሁም በሌሎች ምክንያቶች የተጎዱ የመሰረተ ልማት አውታሮችን መልሶ ከማቋቋም ጎን ለጎን ሀገራዊው ኢኮኖሚያዊ ሁኔታና የኑሮ ውድነት፤ እንዲሁም በልዩ ልዩ ማህበራዊና መንግሥታዊ አገልግሎቶች አሰጣጥ የሚሰማው የሕዝብ ቅሬታ ለሰብአዊ መብቶች ከፍተኛ አደጋና ስጋት በመሆኑ የቅርብ ክትትል የሚሹ ጉዳዮች መሆቸውንም ለአስፈጻሚው በየጊዜው ሲያሳስቡ እንደቆዩ ተናግረዋል፡፡

አንዳንዶቹ ውጤት ሲያመጡ ሌሎቹ በአስፈጻሚው አካል ቸልተኝነት ሳይፈቱ መቅረታቸውን ያስታውሳሉ፡፡

**የግል ሕይወት**


አብራቸው በትግል ከነበረች ጓደኛቸው በ1983 ዓ.ም ትዳር መስርተው አራት ልጆች አፍርተዋል።በጣም የሚያስደስታቸው ራሳቸውን ሆነው መገኘታቸው ነው። ሰው ለማስደሰት ወይ ለማስከፋት ያደረጉት ምንም ነገር እንደሌለ ይናገራሉ። የእርሳቸው መርህ "ለሚስቴ ወይም ለልጆቼ የማልነግራቸው ሀብት ሊኖረኝ አይገባም" የሚል ነው። በንፅሕና መኖራቸው ደስ ያሰኛቸዋል። ይህንን ባላደረግሁ የምለው አንድም ነገር የለኝም ይላሉ። በመታገላቸው ደስተኛ ናቸው። ከህዝብ የተረከቡትን አደራ በተቻላቸው አቅም ሁሉ ለህዝብ ጥቅም አውያለሁ ይላሉ። የሰው ግዴታው መጀመሩ ነው። ይህ ባይሆን ኖሮ የትዳር አጋርህ እንኳ አትመሰክርልህም የሚለው መዝጊያ ቃላቸው ነበር፡፡

ኢኮኖሚ

# ባህልና ቱሪዝም

## ዘርፉን የሚያሻግር የኤኮ ቱሪዝም ልማት

ኃይሉ ሣህለድንግል



የኤኮ ቱሪዝም ጽንሰ ሀሰብ ለኢትዮጵያ የቅርብ ጊዜ መሆኑ ይገለጻል፤ እንዲያም ሆኖ ግን ሀገሪቱ በዓለም አቀፍ ተቋማት ጭምር አድናቆት የተቸራቸው የኢኮቱሪዝም መንደሮች እንዳሏት መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በቅርቡ ደግሞ በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶክተር) አነሳሽነት በገበታ ለሀገር ፕሮጀክት የተገነባው የወንጪ ደንዲ የኤኮ ቱሪዝም መንደር ተመርቋል፡፡

በኤኮ ቱሪዝም ልማት ተዋናይ መሆን ካለባቸው መካከል ልማቱ የሚካሄድበት የአካባቢ ማህበረሰብ አንዱ ነው፡፡ ማህበረሰቡ ከዚህ የቱሪዝም ዘርፍ ከሚገኘው ሀብት ተቋዳሽ እንዲሆን መደረግ ይኖርበታል፤ ራሱም ለቱሪስቶች አገልግሎቶችን በመስጠት ተጠቃሚነቱን ማረጋገጥ ይጠበቅበታል፡፡

በወንጪ ደንዲ የኤኮ ቱሪዝም መንደር ግንባታ ወቅትም ይሄው ተጠቃሚነት መታየት ጀምሯል፡፡ የኤኮ ቱሪዝም መንደሩ የተለያዩ ግዙፍ መሰረተ ልማቶች የተገነባለት ሲሆን፣ ለበርካታ የአካባቢው አርሶ አደሮች የመኖሪያ ቤቶች ግንባታዎች ተካሂደዋል፡፡

የኤኮ ቱሪዝም መንደሩን የተመለከቱ መረጃዎች እንደጠቆሙት፤ በወንጪ ደንዲ የኤኮ ቱሪዝም መንደር ግንባታ ወቅት የአካባቢው ወጣቶች ታላላቅ የልማት ስራዎች ይዘው የሚመጡትን የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት ማጣጣም ጀምረዋል፤ በግንባታው ወቅት ከስምንት ሺ እስከ 12 ሺ የሚደርሱ ዜጎች የሥራ እድል አስገኝቷል። ሰፊው የአካባቢው ማህበረሰብም አሁን የላቀ ተጠቃሚነት እድል ማግኘቱን ጠቅላይ ሚኒስትሩ በማህበራዊ ትስስር ገጻቸው ማስታወቃቸውን መገናኛ ብዙኃን በዘገባቸው አመልክተዋል፡፡

መንደሩ ከተገነቡለት መሰረተ ልማቶች መካከልም 43 ኪሎ ሜትር መንገዶች፣ 35 ኪሎ ሜትር የመንገድ መብራትና የኃይል አቅርቦት፣ 72 ሜትር ድልድይ እና የትምህርት ቤት ግንባታዎች ይጠቀሳሉ፡፡ የቴሌኮምና የንጹህ መጠጥ ውሃ መሰረተ ልማትም ተገንብተውለታል፡፡

የኤኮ ቱሪዝም መንደሩን መርቀው የከፈቱት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር ) የወንጪ ደንዲ የኤኮ ቱሪዝም ፕሮጀክት የተለያዩ መሰረተ ልማቶችን ያቀፈ መሆኑን ጠቅሰው፣ ይህም ባለሀብቶች በቀጣይ ለሚሰሩት ሥራ የተመቻቸ ሁኔታ መሆኑን አስታውቀዋል፡፡ ፕሮጀክቱ ጅምር ሥራ ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ በቀጣይ ትልቅ ሥራ ይጠብቀናል ሲሉ አመልክተዋል፡፡

የክልሉ መንግሥት ባለሀብቶች በወንጪ ደንዲ አካባቢ በስፋት ኢንቨስት እንዲያደርጉ በትኩረት መስራት እንዳለበትም አስገንዝበዋል፤ የአካባቢው ማህበረሰብም የአካባቢውን ተፈጥሮ ጠብቆ ያቆየበትን ሁኔታ አጠናክሮ እንዲቀጥልም አስታውቀዋል፡፡

በምረቃ ሥነሥርዓቱ ላይ የተገኙት የአፍሪካ ህብረት ኮሚሽን ሊቀመንበር ሙሳ ፋቂ ማሃማት የወንጪ ደንዲ የኤኮ ቱሪዝም መንደር የኢትዮጵያን ኤኮ ቱሪዝም ከማሳደግ ባለፈ የአፍሪካ ኤኮ ቱሪዝም እንዲያድግ በር ይከፍታል ሲሉ ተናግረዋል። የአካባቢው ማህበረሰብ እንዲለማና እንዲያድግ በማድረግ ትልቅ ሚና እንደሚጫወትም ነው ያስታወቁት፡፡

በወንጪ ደንዲ ኤኮ ቱሪዝም፣ እንደ ሀገር ባለው የኤኮ ቱሪዝም ሀብትና በተያዘው የኢኮ ቱሪዝም ልማት ላይ ያነጋገርናቸው የኢትዮጵያ ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት የቱሪዝም ትምህርት ክፍል መምህር አቶ በቀለ ኡማ፣ በትምህርት ክፍሉ በቱሪዝም ላይ የተለያዩ ፕሮጀክቶችን፣ የምርምርና ጥናት እንዲሁም የማማከር ሥራዎችን ሰርተዋል፡፡ በግሉ ዘርፍም በቱሪዝምና ሆስፒታሊቲ ላይ ድርጅት ከፍተው እየሰሩም ናቸው። በቱር ኦፕሬሽን ቢዝነስ እንዲሁም በቱሪዝም ላይ በሚዘጋጁ ሁነቶች ዝግጅት ላይም ይሰራሉ፡፡

አቶ በቀለ የወንጪ ደንዲ ኤኮ ቱሪዝም መንደርን ምርጥ የቱሪስት መዳረሻ፣ ምርጥ ምሳሌ፣መንግሥት የወሰደው ምርጥ እርምጃ ሊባል የሚችል ነው ሲሉ ገልጸውታል፡፡ መንግሥት በዚህ ላይ የወሰደው እርምጃ ትክክለኛና ወቅታዊ የቱሪዝም አቅጣጫን የጠበቀ ነው ብለዋል፡፡ ‹‹ምክንያቱም በግሉ ዘርፍ የማይሰራውን መንግሥት ከሠራ፣ የግሉ ዘርፍ ደግሞ ማድረግ ያለበትን ካደረገ ሀገሪቱና የአካባቢው ማህበረሰብ ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡ ሁሉም እንደ ድርሻው ከቱሪዝሙ የሚቋደስበት ሁኔታ ይፈጠራል›› ሲሉ አብራርተዋል፡፡

እሳቸው እንዳስታወቁት፤ ሌሎች የኤኮ ቱሪዝም መንደሮች በአርሲ፣ በአማራ ክልል በደቡብ ክልል አሉ። የወንጪ ደንዲ ኤኮ ቱሪዝም መንደር አሁን ትልቅ የቱሪዝም መዳረሻ ቦታ መሆን ችሏል፡፡ በዚህ ልማት የተከናወነውን ምርጥ ሥራ ወደ ሁሉም ክልሎች ማስፋት ያስፈልጋል፡፡

በሀገሪቱ ለኤኮ ቱሪዝም አገልግሎቶች ሊውሉ የሚችሉ በጥናት የተለዩም ያልተለዩም ቦታዎች እንዳሉ ጠቅሰው፣ በእነዚህ ላይ ምርጥ የኤኮ ቱሪዝም ስፍራዎችን መገንባት ከተቻለ ኢትዮጵያ ወደፊት ከቱሪዝም ዘርፉ የምትጠቀመው፣ ቱሪዝም የሚያመጣው አዎንታዊ ገጸ በረከት ብዙ ነው ብዬ አምናለሁ ሲሉም አስታውቀዋል፡፡

ኤኮ ቱሪዝም ለአንድ አካባቢ ብቻ ሳይሆን እንደ ሀገር ያለው ጥቅም ከፍተኛ መሆኑንም መምህሩ ጠቁመው፣ ‹‹ኤኮ ቱሪዝምን ማነው እንዲያለማ የሚጠበቀው፤ መንግሥት ደንዲ ወንጪ ላይ ገንብቷል፤ በቀጣይስ ይህን የመሰለ መሰረተ ልማት ያለው የኤኮ ቱሪዝም መንደር ማነው የሚያለማው?›› ሲሉም ይጠይቃሉ፡፡

ቱሪዝም የእያንዳንዱን ተዋናይ እጅ ለእጅ ተያይዞ መስራትን እንደሚጠይቅ አስታውቀው፣ ይህ ሥራ በአንድ አካል ብቻ የሚሰራ ከሆነ ስራው ጊዜያዊ ይሆናል፤ ዘላቂ የቱሪዝም ልማት ጥቅምን ሊያመጣ አይችልም ሲሉም ያስገነዝባሉ፡፡

እሳቸው እንዳብራሩት፤ በግሉ ዘርፍ የማይደፈሩ፣ የቢሮክራሲ ውጣ ውረድ የሚበዛባቸውና የውጭ ምንዛሬ የሚያስፈልጋቸው ልማቶች አሉ፡፡ ለምሳሌ መሰረተ ልማት መዘርጋት በግሉ ዘርፍ ብቻ አይሰራም። መንግሥት ከደንዲ ወይም ከጊንጪ እስከ ወንጪ ድረስ የአስፋልት መንገድ ሠርቷል፡፡ ይህንን በግሉ ዘርፍ መስራት አይቻልም፤ ወጪው በጣም ከፍተኛ በመሆኑ መንግሥት ይገባበታል፡፡ ይህ አሁን በወንጪ ደንዲ የተጀመረው የኤኮ ቱሪዝም ልማት በጣም ጥሩ ስትራቴጂ ነው የሚሉት መምህሩ፣ የኢትዮጵያን ቱሪዝም አንድ እርምጃ ወደፊት እንደሚያስፈነጥረውም አስታውቀዋል፡፡

ሀገሪቱ ከእነዚህ የቱሪዝም መሰረተ ልማቶች ተጠቃሚ የምትሆነው በመንግሥትና በግሉ ዘርፍ አጋርነት (ፐብሊክ ፕራይቬት ፓርትነርሽፕ) አንድ ላይ ተቀናጅተው ሲሰሩ ብቻ ነው ሲሉም ይመክራሉ፡፡

መንግሥት በወንጪ ደንዲ መሰረተ ልማት ዘርግቷል፤ የግሉ ዘርፍ ደግሞ ሆቴሎችን፣ ሎጂዎችንና ሪዞርቶችን መገንባት ይኖርበታል ያሉት አቶ በቀለ፣ ማህበረሰቡን ከልማቱ ተጠቃሚ የምታደርገው ከሆነ መሰረተ ልማቱን፣ መንደሩን በህይወት የመኖርና ያለመኖር ጉዳይ ያደርገዋል ይላሉ፡፡ ይህ ሲሆን ማህበረሰቡ ለሆቴሎቹም፣ ለሎጆቹም፣ ለመንገዱም፣ ወዘተ ጥበቃ ያደርጋል ብለዋል፡፡

‹‹ይሄ ሆቴል፣ ሎጅና ሪዞርት ቢበላሽ በቀጥታም በተዘዋዋሪም መንገድ የምጎዳው እኔ ነኝ›› የሚል አመለካከት እንዲይዝ፣ ‹‹ጉዳት ቢደርስበት ገጹታው የሚባለሸው የእኔም ነው›› ብሎ እንዲያስብ ማድረግ ላይ መሰራት እንዳለበትም ያመለክታሉ፡፡ በዚህ መልኩ ከተሰራ በቱሪዝም ልማቱ በጣም ብዙ የሚያራምድ፣ ዘላቂ የቱሪዝም ልማትን የሚያመጣ ከልማቱም ማህበረሰቡን ተጠቃሚ የሚያደርግ ይሆናል ሲሉ ያብራራሉ፡፡

‹‹ኤኮ ቱሪዝም ማለት ማህበረሰቡን ያማከለ ቱሪዝም ማለት ነው›› ያሉት አቶ በቀለ፣ ‹‹እንደ እኔ አባባል ኤኮ ቱሪዝም ማለት የማህበረሰቡን ለማህበረሰቡ ማለት ነው ሲሉም ገልጸዋል፡፡ ኤኮ ቱሪዝም ባለቤትነቱ የማህበረሰቡ ነው፤ የአንድ ሰው የሁለት ሰዎች አይደለም ሲሉም ያብራራሉ፡፡

ለኤኮ ቱሪዝም መንደርነት ሊውሉ ለሚችሉ አካባቢዎች መሰረተ ልማት ከተሟላ ማህበረሰቡ የቱሪዝም ምርቶችን፣ ቡና፣ ምግብ፣ ወተት፣ ባህላዊ መጠጦችና የመሳሰሉትን በማቅረብ ተጠቃሚ እንደሚሆን ጠቅሰው፤ ጎብኚዎችም ይህን እንደሚወዱት ይገልጻሉ፡፡

የኤኮ ቱሪዝም አካባቢ ማህበረሰብ ወደ ከተማ ወስዶ የሚሸጣቸው ለምግብነት የሚውሉ እንደ እህል፣ አይብ፣ ወዘተ ያሉ ምርቶች እንዳሉት ጠቅሰው፣ የቱሪዝም መንደሩ በአካባቢው ከተመሰረተ እነዚህን ምርቶች እዚያው አካባቢ ላይ ለጎብኚዎች ሊሸጥ የሚችልበት ሁኔታ ይኖራል ብለዋል፡፡

ከዘላቂ ቱሪዝም ልማት ሀገሪቱም ማህበረሰቡም በዘላቂነት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ከተፈለገ መንግሥትና የግሉ ዘርፍም ተቀናጅተው መስራት እንዳለባቸው ያስገነዝባሉ፡፡ ይህ ካልሆነ የምናልመውና የምናቅደው ቦታ መድረስ አንችልም የሚል እምነት ነው ያለኝ ሲሉም አስታውቀዋል፡፡ በእያንዳንዱ የቱሪዝም መዳረሻ ልማት ሥራ የመንግሥትና የግል አጋርነት መኖር ግዴታ መሆኑን አመልክተዋል፡፡

የግሉ ዘርፍም ኢንዱስትሪው ውስጥ በመግባት መንግሥት ያመቻቸለትን ሁኔታ መጠቀም እንዳለበት አስገንዝበው፣ መንግሥት አንድ እርምጃ ወደፊት ከሄደ የግሉ ዘርፍ ይህን ተቀብሎ ኢንዱስትሪውን የማስቀጠል ኃላፊነት አለበት ብለዋል፡፡

ኤኮ ቱሪዝም በዓለም ደረጃ ከተጀመረ ቆይቷል፤ በኢትዮጵያ የተጀመረው በቅርቡ ነው ያሉት አቶ በቀለ፣ በተለይ ማህበረሰብ ተኮር ኤኮ ቱሪዝም ያላቸው ሀገሮች ብዙ መሆናቸውንም አስታውቀዋል። በኤኮ ቱሪዝም ላይ እየሰሩ ካሉ የእስያ ሀገሮች ህንድና ኢንዶኔዢያን ጠቅሰው፣ የእነዚህ ሀገሮች ማህበረሰቦች በዚህ የቱሪዝም አይነት ገፅታቸውን ይገነቡበታል፤ ባህላቸውን ይሸጡበታል ሲሉ አብራርተዋል፡፡ በአፍሪካም እንደ ኬንያ፣ ኡጋንዳና ታንዛኒያ ባሉት ሀገሮች እንደሚሰራበት አስታውቀዋል፡፡

እሳቸው እንዳሉት፤ የኢትዮጵያ መንግሥትም በዚህ ላይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ መሥራት ጀምሯል፤ በዚህ ላይ የግሉ ዘርፍም ሊሳተፍበት ይገባል፤ ሀገሪቱ ጥሩ ጥሩ የኢኮ ቱሪዝም ቦታዎችን ማልማት ትችላለች፤ ይህም ሀገሪቱ የቱሪዝም ዘርፍ ከሚያመጣቸው አዎንታዊ ጥቆሞች እንድታገኝም ያስችላል፡፡

ማህበረሰብ ባለበት ቦታ ሁሌም ኤኮ ቱሪዝም አለ፤ በተለይ ከከተማ ራቅ ብለው የሚኖሩ ማህበረሰቦች ባሉባቸው አካባቢዎች እምቅ አቅሙ ይኖራል፤ በዚህም ላይ ትንሽ ሀብት በማውጣት አካባቢውን መዳረሻ በማድረግ፣ በዚህም በርካታ ቱሪስቶችን በማሰብ የአካባቢውን ማህበረሰብም ሀገርንም ከቱሪዝም ዘርፉ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ ይቻላል፡፡

ለኤኮ ቱሪዝም በሚሆን አካባቢ ላይ ብዙ ወጪ ማድረግ አያስፈልግም፤ ማህበረሰቡም መስህቡም እዚያው ያሉ ናቸው ያሉት መምህሩ፣ ማህበረሰቡም መስህቡም ከየትም አልመጡም፤ እዚያ የሚደረስበት፣ በዚያ አገልግሎት የሚሰጥበት ሁኔታ ብቻ ነው የተፈጠረው ብለዋል። ለምሳሌ ወንጪ ስምንት ቁጥሩ /ሀይቁ/ እዚያው የነበረና ያለ ነው፤ ማህበረሰቡም እዚያ ያለ ነው፤ በፈረስ መጓዝና የመሳሰሉትም እዚያው ያሉ ናቸው፡፡ የተሰራው ይህን ትንሽ ከፍ ማድረግ ላይ ነው ሲሉ አብራርተዋል፡፡ የቱሪስቶችን ምቾት ከመጠበቅና ከመሳሰሉት አኳያ ሆቴሎችን፣ ሪዞርቶችን ፣ ሎጆችን፣ የመንገድ፣ የውሃ የቴሎኮምና በመሳሰሉት ላይ ኢንቨስት ማድረግ ነው የሚያስፈልገው ብለዋል፡፡

መምህሩ ሌላው ለዘርፉ አስፈላጊ ብለው የጠቀሱት ሰላምና ደህንነት ነው፡፡ እንደ አሳቸው ማብራሪያ፤ ቱሪዝም ሲታሰብ በቅድሚያ ወደ አእምሮ የሚመጣው የሰላምና ጸጥታ ጉዳይ ነው፤ ቱሪዝም ማለት የሰዎች ጉዞ፣ እንቅስቃሴ ነው፤ ሰዎች ከቦታ ወደ ቦታ ይንቀሳቀሱበታል፡፡ ስለቱሪዝም ሲወራ ስለሰዎች እንቅስቃሴ ነው የሚወራው፡፡

ሰዎች ከቦታ ወደ ቦታ ሲንቀሳቀሱ በቅድሚያ ወደ አእምሯቸው የሚመጣው ብርና ጊዜ ያላቸው መሆኑ ብቻ አይደለም ሲሉም ጠቅሰው፤ በቅድሚያ ወደ አእምሯቸው የሚመጣው የአካባቢው ደህንነትና ጸጥታ ጉዳይ ነው ይላሉ፡፡ ለእዚህም የአካባቢ ደህንነትና ጸጥታ በደንብ መጠበቅ ይኖርበታል ሲሉ አስገንዝበዋል፡፡ እሱ በመንግሥትም በግሉ ዘርፍም መሰራት እንዳለበት ጠቁመው፤ በተለይ በኛ ሀገር በትናንሽ ነገሮች የሚነሱ ችግሮችን መፍታት ከቻልን በቱሪዝም ዘርፉ ጥሩ መስራት እንችላለን ብዬ አስባለሁ ብለዋል፡፡

ስፖርት እና መዝናኛ

# ሳምንቱን በታሪክ

## የአጼ ዮሐንስ ንግሥና

**ዋስልኝ አየለ**

በዚህ ሳምንት ብዙ የታሪክ ክስተቶች አሉ። የአጼ ዮሐንስ አራተኛን የንግሥና ሳምንት ምክንያት በማድረግ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ የነበራቸውን ሚና እናስታውሳለን። ከዚያ በፊት ግን ሌሎች የዚህ ሳምንት ክስተቶችን እናስታውስ፡፡

ከ62 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ጥር 13 ቀን 1954 ዓ.ም ኢትዮጵያ በታሪኳ እስካሁን ድረስ ብቸኛ የሆነውን የአፍሪካ ዋንጫ አሸነፈች፡፡

ከ14 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ጥር 15 ቀን 2002 ዓ.ም 90 ሰዎችን (82 መንገደኞችንና 8 ሰራተኞችን) ይዞ ከቤሩት፣ ሊባኖስ፣ ራፊቅ ሃሪሪ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ ተነስቶ ወደ አዲስ አበባ እየበረረ የነበረው የበረራ ቁጥሩ ET409 የሆነ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ቦይንግ 737-8AS አውሮፕላን ሜዲትራኒያን ባሕር ላይ ወደቀ፤ በአውሮፕላኑ ውስጥ የነበሩት ሁሉም ሰዎች ሞቱ፡፡

ከ100 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ጥር 16 ቀን 1916 ዓ.ም የኢትዮጵያና የኢትዮጵያውያን ባለውለታ የነበሩት ዶክተር ካትሪን ሐምሊን ተወለዱ፡፡ እነሆ ዘንድሮ 100ኛ ዓመታቸው ሆነ፡፡

ከ53 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ጥር 17 ቀን 1963 ዓ.ም በዓለም ታሪክ ከታዩ አምባገነን ገዢዎች መካከል አንዱ እንደነበር የሚነገርለት ኢዲ አሚን ዳዳ ጠቅላይ ሚኒስትር ሚልተን አቦቴን በመፈንቅለ መንግሥት ገልብጦ የኡጋንዳን ስልጣን ጨበጠ፡፡ በወቅቱ ጠቅላይ ሚኒስትር ሚልተን አቦቴ በሲንጋፖር በሚካሄደው የጋራ ብልጽግና ሀገራት ጉባዔ ላይ እየተሳተፉ ነበር፡፡ ኢዲ አሚን ዳዳ እነሆ በታሪክ ውስጥ የአምባ ገነን ምሳሌ ተደርጎ ይታወሳል፡፡

ከ137 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ጥር 18 ቀን 1879 ዓ.ም በጀግናው ራስ አሉላ እንግዳ (አሉላ አባነጋ) የተመራው የኢትዮጵያ ጦር የኢትዮጵያን ድንበር ጥሰው የመጡትን ጣሊያኖችን ‹‹ዶጋሊ›› በተባለ ቦታ ላይ ገጥሞ ዶጋ አመድ አደረጋቸው፡፡

ከ33 ዓመታት በፊት ጥር 18 ቀን 1983 ዓ.ም ኢትዮጵያን በግፍ የወረሩት፤ ሦስተኛው የሶማሊያ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዝደንት የነበሩት ሜጀር ጀኔራል መሐመድ ዚያድ ባሬ ከስልጣን ተባረሩ፡፡

ከ79 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ጥር 19 ቀን 1937 ዓ.ም ናዚ ጀርመንና ተባባሪዎቻቸው በርካታ ሰዎችን፤ በተለይም አይሁዶችን ሲያሰቃዩበት የነበረውና ከ1.1 ሚሊዮን በላይ ሰዎችን (960 ሺህ አይሁዶች፣ 74 ሺህ አይሁድ ያልሆኑ ፖላንዳውያን፣ 21 ሺህ ሩማንያውያን፣ 15 ሺህ የሶቭየት ኅብረት ምርኮኛ ወታደሮች እንዲሁም 15 ሺህ ሌሎች አውሮፓውያን) የገደሉበት ‹‹የኦሽዊትዝ ካምፕ›› በሩስያ ቀዩ ጦር ነፃ ወጥቶ ተዘጋ፡፡

አሁን ደግሞ ከ152 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ጥር 13 ቀን 1864 ዓ.ም የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ሆነው የነገሡት ወደ አጼ ዮሐንስ 4ኛ ታሪክ እንለፍ፡፡

አጼ ዮሐንስ 4ኛ የተንቤንና የእንደርታ ባላባቶች ከነበሩት ወላጆቻቸው ሐምሌ 5 ቀን 1825 ዓ.ም ‹‹ማይ በሀ›› (ተምቤን) በሚባል ሥፍራ ተወለዱ። ከመንገሣቸው በፊትም ‹‹ርዕሰ መኳንንት ደጃዝማች በዝብዝ ካሳ›› በመባል ይታወቁ ነበር። በወቅቱም በትግራይ መኳንንት እግር ተተክተዉ የአካባቢዉ ገዢ ሆነዉ ቆይተዋል።

በሰሜን በኩል በወደቡ አቅራቢያ መገኘታቸውም ከአውሮፓውያን ቆንሲሎች ጋር ወዳጅነት እየመሰረቱ መጠነኛ የትጥቅ ድጋፍ እንዲያገኙ አስችሏቸዋል። ደጃዝማች ካሳ ምርጫ የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገሥት እንደሚሆኑ እርግጠኛ ስለነበሩ ‹‹ደጃዝማች›› ከነበሩበት ጊዜ ጀምሮ ራሳቸውን ለውጭ ሀገራት መንግሥታት በደብዳቤ ያስተዋውቁ ነበር።

ንጉሰ ነገሥት ዳግማዊ አጼ ቴዎድሮስ መቅደላ ላይ ከሞቱ በኋላ ለሦስት ዓመታት ያህል የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት የነበሩት አፄ ተክለጊዮርጊስ፣ ደጃዝማች ካሳን ሊያስፈራሩ አንድ ስልቻ ጤፍ አስቋጥረው ‹‹የሰራዊቴ ቁጥር እንደዚህ የበዛ ነውና አትችለኝም፤ ስለዚህ ገብር!›› ብለው ላኩባቸው፡፡ ደጃዝማች ካሳ ደግሞ በምላሹ የተላከውን ጤፍ አስቆልተው ‹‹የእኔ ሰራዊት ደግሞ ያንተን ሰራዊት እንደዚህ ይቆላዋል›› ብለው ላኩላቸው፡፡ የተናገሩት አልቀረም፤ ደጃዝማች ካሣ አፄ ተክለ ጊዮርጊስን ዓድዋ አካባቢ ‹‹አሰም›› በሚባል ሥፍራ ላይ ሐምሌ 5 ቀን 1863 ዓ.ም ተዋግተው ድል አደረጓቸው፡፡

ከድሉ በኋላም ለበዓለ ንግስናቸው የሚያስፈልገውን ሁሉ ሲያደራጁ ቆይተው ጥር 13 ቀን 1864 ዓ.ም በእለተ እሁድ በአክሱም ፅዮን ቤተ ክርስቲያን በጳጳሱ አቡነ አትናቴዎስ እጅ ተቀብተው ‹‹ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ ግርማዊ ዮሐንስ ራብዓዊ ስዩመ እግዚአብሔር ንጉሰ ፅዮን ንጉሰ ነገስት ዘኢትዮጵያ›› ተብለው ነገሡ።

ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ለሀገራቸውና ለሃይማኖታቸው ባላቸው ቀናኢነት የሚታወቁት አጼ ዮሐንስ 4ኛ፣ አንዲት ጠንካራ ሀገር እውን እንድትሆን ያለ ዕረፍት ሲተጉ ኖረዋል። በተለያዩ አቅጣጫዎች ሀገር ለመውረር ከመጡት ከግብጾች፣ ከቱርኮች፣ ከጣሊያኖችና ከደርቡሾች (መሐዲስቶች) እና ከሌሎች የውጭ ኃይሎች ጋር ተደጋጋሚ ጦርነቶችን አድርገው ነፃ ሀገርን ለቀጣዩ ትውልድ ያስረከቡ ትጉህ ንጉሥ እንደሆኑ የታሪክ ሰነዶች ያሳያሉ፡፡

የአጼ ዮሐንስ አራተኛ ታሪክ ሲነሳ በብዙዎች ዘንድ ቶሎ የሚታወሰው ለሀገራቸው ክብር መስዋዕት የሆኑበት የመተማ ጦርነት ነው፡፡ የዚህን ጦርነት ክስተቶች እናስታውስ፡፡

አጼ ዮሐንስ ገላባትን፣ ብሎም አምድሩማንንና ካርቱምን በመያዝ የድርቡሽን መንግሥት ለመገርሰስ ዝግጅት መጀመራቸው ሱዳን ውስጥ ጭምጭምታ ተሰማ። አጼ ዮሐንስ በዋነኞቹ የጦር መሪዎች በእነ ራስ አርአያ ድምፁ፣ ራስ ሚካኤል (መሐመድ አሊ)፣ ራስ ኃይለማርያም ጉግሳ፣ ራስ አሉላ፣ ስልሕ ሻንቆ እና ሌሎችም ታላላቅ የጦር አዛዦች የሚንቀሳቀሱ ክፍለ ሠራዊቶችን በመምራት በቅድሚያ ገላባትን ለመያዝ ዝግጅት በማድረግ ላይ መሆናቸው ወሬው በደርቡሽ ዘንድ ተሰማ።

የገላባቱ ምሽግ ዋና አዛዥ ሸክ በኪ ጡማል በመምጣት ላይ ያለውን ጠላት ከምሽግ ውስጥ ሆኖ መዋጋት ወይስ ገና ከመንገድ ላይ መቁረጥ የትኛው እንደሚሻል አማካሪዎቹን አወያየ። ካለምንም ማወላወል ምሽጋቸውን ማጠናከር አማራጭ የሌለው ዘዴ መሆኑ እርግጥ ነበር። እንደማዕበል የሚነጉደውን የኢትዮጵያ ሠራዊት ከምሽግ ወጥቶ መመከት የማይታሰብም የማይሞከርም ነበር።

አጼ ዮሐንስን ለመግጠም የተመደበው የዘኪ ጥምር ጦር 80,000 ደርሷል። ከቁጥሩ በላይ ጦሩ ምሽጉን አጥብቆ በመያዝ የመጣበትን ጦር ለመመከት ቁርጠኛ ነበር። አዋጅ ነጋሪዎች በገጠር በከተማው እየዞሩ ሱዳናዊ ሁሉ የዕለት ተግባሩን ትቶ ጠብመንጃውን አንግቶ፣ ጎራዴውን ታጥቆ ሀገሩን እንዲከላከል የመሪያቸውን ትዕዛዝ አሰሙ። በሌላ በኩል የኢትዮጵያ መንግሥት የዘመቻ ዝግጅት ከተነገረው በላይ ተጠናክሮ መቀጠሉን የድርቡሽ ወታደራዊ ምንጮች ገለፁ። እነዚህ ወደ ኢትዮጵያ በመግባት መረጃዎችን ያሰባስቡ የነበሩ ሰላዮች የኢትዮጵያን ሠራዊት እንቅስቃሴ በሚከተለው መልክ አቀረቡት።

‹‹የሀበሻ ሠራዊት እንደሰማይ ከዋክብት እንደባህር አሸዋ ህልቆ መስፈርት የለውም። ሠራዊቱ ሲርመሰመስ ለዓይን እይታ የሚታክት፣ መጨረሻው ከአድማስ ባሻገር የሆነ፣ የዘመቻው ንቅናቄ በሚያስነሳው ምድራዊ ደመና ጸሐይን ያጠቆረ አስፈሪ ኃይል ነው››

ይህ ደማቅ ወታደራዊ ዘገባ የድርቡሾች ዋና ከተማ የነበረችውን አምድሩማንን ከወዲህ ወዲያ በሽብር አናወጣት። ከዕለታት አንድ ቀን ሱዳን በሀበሻ እንደምትተፋ፣ የንጉሡ ፈረስም ኮቴው በፈሰሰው ደም ተውጦ፣ እንደ ወሬ ነጋሪ ከጥፋት በተረፈችው አንዲት ዛፍ ጥግ ታስሮ እንደሚታይ እንደ ትንቢት የሚነገረው አፈ ታሪክ ጊዜው መድረሱና ትንቢት የተነገረለት የሀበሻ ንጉሥ ዮሐንስ እንደሆነ ትንቢት ተናጋሪዎች አስረዱ።

በ1881 ዓ.ም ወርሀ የካቲት መጨረሻ ላይ ንጉሠ ነገሥቱ አጼ ዮሐንስ 4ኛ ጎንደር ከተማን ለቀው በመውጣት ሕዝብን ለማጥፋት የተነሳውን ቁርጠኛ ጠላት ለመደምሰስ ሠራዊታቸውን በረድፍ በረድፍ አስከትለው ወደ ገላባት ተመሙ። ከከተማዋ አቅራቢያ እንደደረሱ አጼ ዮሐንስ እንዲህ አሉ፡፡

‹‹እንደ ሌባ ተሽሎክልኮ መጣ እንዳትለኝ፤ ለፍልሚያው ተነስቻለሁና ተነስ!›› ብለው ለድርቡሹ አዋጊና የጦር አዛዥ መልዕክት ሰደዱለት፡፡ ከኢትዮጵያ ሠራዊት ጋር ከወንዶቹ ሌላ በርካታ ቁጥር ያላቸው ወይዛዝርት አብረው ተሰልፈዋል። እነዚህ ሴት ዘማቾች የትዳር ጓደኞቻቸውን፣ የእጮኞቻቸውን፣ የወንድሞቻቸውንና የአባቶቻቸውን የሞትና የመከራ ጽዋ ለመቅመስ ኑሯቸውን በትነው፣ ጎጇቸውን ዘግተው ወደ ጦር ሜዳ የዘመቱ ናቸው።

ቅዳሜ መጋቢት 1 ቀን 1881 ዓ.ም አፄ ዮሐንስ የገላባትን ምሽግ ማጥቃት ጀመሩ፡፡ ሠራዊታቸው መሪውን እየተከተለ ከምሽጉ ውስጥ በፉከራና በቀረርቶ እየዘለለ ገባ። ከጦር አውድማው የሚነሳውን አቧራ አውሎ ነፋሱ ሲያነሳው እሽክርክሪት እየሰራ በውጊያው መሀል ሰይጣናዊ ጭፈራውን አቀለጠው። ከወዲያም ከወዲህም በሙቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ለዘመን ፍጻሜ የሚዋደቁ የሚመስሉ ወታደሮች አንዱ ሌላውን ለመለየት በማይቻልበት ሁኔታ ወደቁ፡፡ የሞትና ሽረት ትግሉ የቀኑን ብርሃን ጽልመት አለበሰው።

ንጉሠ ነገሥት አጼ ዮሐንስ ጦርነቱ መሐል ገብተው ሲዋጉ ያየው የኢትዮጵያ ወታደር መንፈሱ በአንዳች ወኔ እየተፈነቀለ ግስጋሴውን ቀጠለ። የድርቡሾች ጠንካራ ምሽግ መላላትና መሳሳት ጀመረ።

ከድርቡሾች ሰይፍና የጥይት አረር ይልቅ የኢትዮጵያ ጦርን የከበደው ቢኖር በአገር ምድሩ የበቀለው እሾህማ ጥቅጥቅ የቆላ ግራር ነበር። ለደርቡሾች ተደራቢ ምሽግ ሆነላቸው። ሀበሾቹ ግራሩን ግራ ቀኝ ረግጠው እየዘለሉ፣ አንዳንድ ጊዜም እያቃጠሉ ወደ ዋናው የደርቡሽ ማዘዣ ጣቢያ ዘልቀው ለመግባት ሲዋጉ የድርቡሽ ሠራዊት አጋጣሚውን በመጠቀም ጥይቱን አርከፈከፈው። በዚህ የትንቅንቅ ሰዓት ነበር ከማህዲ ሰፈር አምልጠው ለኢትዮጵያ ሠራዊት እጃቸውን የሰጡ ትኹሪሮች (ደቡብ ሱዳናውያን) ጠቃሚ መረጃ የሰጡት።

በደርቡሾች የጦር ሰፈር ደካማው የውጊያ ግንባር ያለበትን ምርኮኞቹ ተናገሩ። የኢትዮጵያ ሠራዊት ለመጨረሻው የሞት ሽረት ድል ወጊያውን አፋፋመ፡፡

በሁለቱም ወገን ከተከፈለ ከባድ የሕይወት መስዋዕትነት በኋላ የኢትዮጵያ ሠራዊት እንደ ውቅያኖስ ማዕበል እያስገመገመ ከፊት ለፊቱ የቆመውን ሁሉ እየደመሰሰ የደርቡሾችን ወታደራዊ እምብርት ዘልቆ በመግበት የበላይነቱን ተቀዳጀ። ድልን ጨብጦ በመገስገስ ላይ የነበረውን ኃይል በተመለከቱ ጊዜ ከኋላ ሆነው ‹‹ግፋ በለው›› እያሉ እልል ሲሉ የዋሉት በሺዎች የሚቆጠሩ የደርቡሽ ሴቶች ልብ የሚነካ እዬዬና ዋይታ ያሰሙ ጀመር።

የኢትዮጵያ ጦር አሁንም ማጥቃቱን በመቀጠልና ያገኘውን ድል በማጠናከር የድርቡሾችን ምሽግ ሙሉ በሙሉ ተቆጣጠረ። ይህ ግስጋሴ ሀበሾችን ወደ ፍፁም ድል በር የሚያደርሰው ወሳኝ እርምጃ ነበር።

የገላባት (መተማ) ጦርነት ከዚያም ከዚህም የሰው ልጅ እንደ ቅጠል ቢረግፍበትም ድል ፊቷን ወደ ዮሐንስ ማዞሯ አጠራጣሪ አልነበረም። ሐበሾች የደርቡሽን የትጥቅና ስንቅ ማከፋፈያ ማዕከልን ተቆጣጠሩ። የጦር አዛዡ አቡ አንጋ ጦርነቱን ይመራ የነበረው ከዚሁ ሠፈር ሆኖ ነበርና የዮሐንስ ወታደሮች የማዘዣ ጣቢያው መደምሰስን ተከትሎ የደርቡሾችን የሬሳና የቁስለኛ ክምር በማገላበጥ የራሱን የአቡ አንጋን አስከሬን ለማግኘት ፍለጋ ጀመሩ።


ከማዘዣ ጣቢያቸው ሙሉ በሙሉ መደምሰስና ትጥቅና ስንቃቸው በኢትዮጵያ ሰራዊት መማረክ በኋላ የድርቡሾች ወኔ ሟሸሸ። የደርቡሽ ጦር በእጁ የያዘው ጥይትና ሌላ አስፈላጊ የውጊያ መሣሪያ አልቆ መዋጋት በማይችልበት ደረጃ ላይ በመድረሱ የዮሐንስ ዘማች ኃይል አሸናፊነት እርግጥ ሆነ።

ደርቡሾች ተሸንፈው ‹‹እግሬ አውጭኝ›› እያሉ በሚሸሹበት ሰዓት ንጉሠ ነገሥት አጼ ዮሐንስ በአንዲት ጥይት ተመትተው መውደቃቸው በኢትዮጵያውያን ሰፈር ተሰማ። ወሬው እየተቀጣጠለ ጦሩን ግራ አጋባው፡ ፡ በድርቡሽ ቆራጥነት ያልተፈቱት ሀበሾች በድል አፋፍ ላይ ቆመው የድርቡሽን ሽሽት አሻግረው በሚመለከቱበት ሰዓት በንጉሠ ነገሥታቸው መመታት ድንጋጤ ጥርጣሬና ተስፋ መቁረጥ ወረራቸው። ከድል በኋላ በንጉሠ ነገሥቱ ላይ በተተኮሰችው ጥይት ምክንያት የኢትዮጵያውያኑ ሠፈር ተስፋ መቁረጥና ትካዜ ገባበት። ካለ መሪ ካለ አስተባባሪ የቀረው የኢትዮጵያ ሠራዊት ፊቱን ወደ አገሩ በማዞር ጉዞ ጀመረ። ድል ፊቷን ወደ ኢትዮጵያውያን ብታዞርም እንደገና ወደ ድርቡሽ ዞረች፡፡

የተበታተኑት የድርቡሽ ሠራዊቶች እየተሰበሰቡ ወደ ተደመሰሰው ምሽጋቸው መመለስ ጀመሩ። በዚህ ሁኔታ ድል የቀናው የድርቡሽ ሠራዊት የአጼ ዮሐንስ አራተኛን ራስ ቆርጦ ለመውሰድ ዕድል አገኘ፡፡

የአፄ ዮሐንስ ራስ በአምድሩማን አደባባይ ለዕይታ ቀርቦ እንደበቃ በቆዳ ተለብዶ ወደ ደንጎላ (ዳርፉር ግዛት) ከዚያም አልፎ እስከ ግብጽ ድንበር ድረስ በግመል ተጭኖ እንዲወሰድ ተደርጓል፡፡ እነሆ ዛሬ ድረስ ይህ ታሪክ በጠላትም ሆነ በወዳጅ ወገን ይነገራል፡፡

አጼ ዮሐንስ 4ኛ ከነገሥታቱ ለየት የሚያደርጋቸውም ይህ ታሪካቸው ነው፡፡ ንጉሥ ሆነው ልክ እንደ ተራ ወታደር ሲዋጉ ነው የሞቱት። እንደ አገር ባላቸው ታሪክ ደግሞ ኢትዮጵያ አገራቸውን የማያስደፍሩ ጀግኖች አገር መሆኗን አሳይተዋል፡፡ የጀግኖችን ታሪክ የምናስታውሰውም ለዚህ ነው፡፡


አጼ ዮሐንስ 4ኛ

# የዝነኞች ገጽ

# ሁለቱ እጥፋቶች

**ሙሉጌታ ብርሃኑ**

ሁለት እጥፋት አንድም ከጋዜጠኝነት አንድም ከቴሌቪዥን መስኮት፤ ከመዝናኛው ቤት ሞት ጭካኔው ከፋ፡፡ ሞት ሆይ ስለምንስ አንዣበብክ አይባልም፤ ምክንያቱም መወለድ ካለ ሁሌም ሞት አለና፡፡ አንዳንድ ጊዜ ግን አያያዝና አወሳሰዱ ሲታይ `ሞት ምነው? አሁንስ መካሪ አጣህሳ' ያስብላል፡፡ ልክ እንደዚህ በአንድ ጀንበር እንደሱናሚ ሲያናውጽ። በዚሁ በያዝነው የወርሀ ጥር ላይ ከሀገራችን ዝነኞች የሕይወት ጓዳ የደገሰው ድግስ መልካም አልነበረም። ሁለት ብርቱዎች፤ በሁለት እጥፋት አንድ ሞት ይዟቸው ነጎደ፡፡

ባጋመስነው የጥር ወር ሀዘን በፊታችን ጥላውን አጥልቶ ልባችንን በመጥፎ የትውስታ ድባቤ ከወቁን ነገሮች አንደኛው የአስፋው መሸሻ የሞት ዜና ነበር። ሞት አይቀሬው፤ ሸምጥ የጋለበ ዕለት ማን ችሎ ማንስ ደፍሮ ይመልሰዋል፡፡ ደግነቱ የወሰደውን ሰው ሥራና ትዝታ ከትውስታ ማህደራችን የመፋቅ አቅም የለውም። ከሬዲዮ ጣቢያ የሰማነው ያ የሚያስገመግም ድምጽ፤ ከቴሌቪዥን መስኮት አፍ ከፍተን የተመለከትነው ጨዋታና እስከ ዕለተ ሞቱ ያልተለየውን ውብ ፈገግታው፤ ከፊታችን ድቅን እያለ በሀዘን ልብን ማስቆዘሙ አይቀርም፡፡ አስፋው መሸሻን የወለደችው አዲስ አበባ ብትሆንም ያሳደገው ግን ብዙ ነው፡፡ ሐምሌ 19 ቀን 1959 ዓ.ም በአዲስ አበባ፤ ዶሮ ማነቂያ መንደር ውስጥ ነበር የተወለደው፡፡ የኋላ ላይ ትንሽ ልጅ ሳለ፤ ከአዲስ አበባ ለቆ በሐረር ከተማ ውስጥ ባለ ትምህርት ቤት የተማረበት አጋጣሚም አለ፡፡ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርቱን እንዳጠናቀቀ ግን ባህር ተሻግሮ፤ ድንበር ዘሎ ከሀገር ወጣ፡፡ ብቻውን አልነበረም፤ ከቤተሰቡ ጋር እንጂ፡፡ አባቱ መሻሻ የታወቁ እንደራሴ ነበሩ፡፡ በወቅቱ ያገለግሉ በነበረበት የአፍሪካ ህብረት ተልዕኮ ምክንያትም 1972 ዓ.ም ወደ ታንዛኒያ በመዘዋወራቸው አስፋውን ጨምሮ ቤተሰባቸውን ይዘው ወደዚያው አቀኑ፡፡ አስፋውም `ኑሮ በታንዛኒያ' ብሎ የሁለተኛ ደረጃ እንዲሁም የኮሌጅ ትምህርቱን በማጠናቀቅ የመጀመሪያ ዲግሪውም በኮምፒውተር ሳይንስ ላይ አረፈ፡፡ በኋላም ከቤተሰቡ ጋር ከታንዛኒያ ወደ ኬንያ ናይሮቢ በማምራት ለጥቂት ዓመታት ያህል ከዚያ ቆይቶ በ1984 ዓ.ም ወደ ሀገሩ ተመልሶ ያቆማትን የሐረር ኑሮ ጀመረ፡፡

አስፋውንና አዲስ አበባን ዳግም ያገናኘው ለመጀመሪያ ጊዜ የሠራበት "ፕሬስ ዳይጀስት" የተሰኘው መጽሔት ነበር፡፡ ከተወሰነ የመጽሔት ቆይታው በኋላ በ1992 ዓ.ም ወደ ሌላኛው አዲስ መንደር ተሸጋገረ። በኢትዮጵያ የመጀመሪያው የሆነው ኤፍ ኤም 97.1 የሬዲዮ ጣቢያ ስርጭቱን የጀመረው በዚሁ ዓመት ነበርና አስፋውም የሙያ ችሎታውን ይዞ ተቀላቀለ። በዚህም፤ ከቅርብ ጓደኛው ዳንኤል ግዛው ጋር በመሆን "አይሬ" የተሰኘ የመዝናኛ ዝግጅት ማቅረብ ጀመሩ። ዝግጅቱም ሆነ ሁለቱ አቅራቢዎች በአድማጩ ሕዝብ ዘንድ ተወዳጅነትና ታዋቂነትን ለማግኘት ጊዜ አልፈጀባቸውም ነበር፡፡ አስፋው፤ በሬዲዮ ጣቢያው የአይሬ መዝናኛ ለስድስት ዓመታት ያህል ከዘለቀ በኋላ፤ ጣቢያውን ለቆ ወደ ዛሚ ሬዲዮ አመራ። ቀጣዮቹንም የሕይወቱን ጥቂት ዓመታት በዚያው አደረገ፡፡ አስፋው መሸሻ ኑሮውን በአሜሪካን ሀገር ያደረገው የዛሬ 14 ዓመታት ገደማ ነበር፡፡ ከዚህ በኋላ ነበር ቀድሞም የነበረውን የዝነኝነት ካባ ደርቦ ለመልበስ የቻለው፡፡ እውቁን ስሙንና አስገምጋሚውን የሬዲዮ ድምጹን ባይረሱትም፤ ብዙዎች በደንብ የተዋወቁት ግን በኢቢኤስ የቴሌቪዥን መስኮት ብቅ ሲል ነበር፡፡ የቴሌቪዥን ጣቢያው ሲቋቋም፤ መርቀው ከከፈቱ ነባር የሚዲያ ሰዎች አንደኛው አስፋው ነው። በወቅቱ በነበረው የሥራ ድርሻ፤ ኢትዮጵያዊያን በስደት፤ በሀገረ አሜሪካ የሚደርስባቸውን የሕይወት ውጣውረድና ስኬት የሚዳስሰው "ኑሮ በአሜሪካ" የተሰኘውን ዝግጅት በማቅረብ ለዓመታት ቆይታ አደረገ፡፡ የአዲስ አበባ የናፍቆት አባዜ አይለቀውምና ተመልሶም ወደ ሀገሩ መጣ፡፡ አሁን ደግሞ ይበልጥ ፍካቱ ጨመረ፡፡ "እሁድን በኢቢኤስ" በተሰኘው የእሁድ የመዝናኛ ዝግጅት ላይ ከሌሎች አጋሮቹ ጋር በመሆን፤ በአስተዋዋቂነት "ሞቅ! ደመቅ! ሸብረቅ!" እያለ በመሪነት ከተፍ አለ፡፡ ከቃላቱ ጋር ስሜት እየፈነጠቁ፤ በአዝናኖት ማሞቅ ማሸብረቁ እንደሆን የእርሱ የራሱ የግሉ ንብረት ነውና በዝነኝነቱ ላይ ፍቅርና ክብርን ደረበበት፡፡ 14 ዓመታት በኢቢኤስ፤ 27 ዓመታት በመዝናኛ ዝግጅት ስሙን ሰቀለበት፡፡

አስፋው "መሸሻ ይሙት!" ካለ በቃ እውነቱን ነው፤ በዚህ መሀላ እውነት ከፍቅር ጋር ቆመው ምስክርነትን ይሰጣሉ፡፡ አባቱን ሲወድ መቼም አይጣል ነው፤ መሸሻ የሚለውን ስም ሳይጠራ ውሎ አያድርም፡፡ "በመሸሻ ሞት!" ካለም በቃ አስፋው በነገሩ በጣሙን ተገርሟል፤ አሊያም ግራ ተጋብቷል ማለት ነው፡፡ ዳሩ ምን ያደርጋል፤ የሚወደውን አባቱን ከሚወዳት ባለቤቱ ጋር በአንድ ቀን በአንድ ጀንበር በመኪና አደጋ አጣቸው፡፡ ከዚህ በላይ እጥፋት፤ ከዚህ በላይ ስብራት ምን አለ? በሕይወቱ እጥፋት ላይ መቼም ከአይንና ከልብ የማይጠፋ ጥቁር ነጥብ ያረፈበት የእርሱ መጥፎው ጊዜ ይሄው ነበር፡፡ ሳይደግስ አይጣላምና በሞት ካጣት ባለቤቱ ሱዛን ባገኘው አንዲያ ልጁ በሳምሶን አስፋው (ጃፒ) ለመጽናናት እየሞከረ ኖረ። አስፋው መሸሻ ደግነቱ ወሰን አልባ ልቡ የቅንነት አርማ ነበር፡፡ ከህልፈቱ በኋላ ዕውቁ ተዋናይ ሰለሞን ቦጋለ በአንድ የቴሌቪዥን ዝግጅት ላይ ቀርቦ እንዲህ አለ፤ "አስፋው የተለየ ፍጡር ነው፡፡ የአባቱ ስጦታ የሆነውና የሚወደውን መኪና ለልብ ህሙማን ህጻናት ለሚሰራው ሆስፒታል በእርዳታ ሰጥቷል። ለመስጠት እንደሚፈልግ ከነገረኝ በኋላ መኪናዋ እድሳት ተደርጎላት በጨረታ እንድትሸጥ ወስነን ነበር፡፡ በጽኑ ከመታመሙ ቀደም ብሎ፤ አንድ ቀን ምሽት ላይ ደወለልኝ፡፡ እናም `እባክህን እሺ በለኝና የመኪናውን ሊብሬ ላስረክብህ፤ የሚሆነው አይታወቅምና በቶሎ ከእጄ ቢወጣ ይሻላል' ሲል ለዚህ ሆስፒታል ምን ያህል ጉጉት እንዳደረበት በደግነቱ ውስጥ አሳይቶኛል። ሆስፒታሉ ስራው ተጀምሮ ሲጠናቀቅ ውለታውን አንረሳምና ስሙን በትልቁ የምናኖርበት ይሆናል" በማለት በቅርብ የሚያውቀውን ወዳጁን ቸርነት መስክሯል፡፡ በዚህ ብቻም ሳይሆን ካለው ሁሌም ቢሆን ከመስጠት በረከት አይጎድልም፡፡ የነበረበት የጭንቅላት ካንሰር የሕይወቱን ጫፍ ለማጠፍ በአልጋ ላይ ባዋለው ጊዜ እርሱን ለማዳን ያልተሯሯጠ አልነበረም። ብዙ ደጋግ ኢትዮጵያዊያን፤ ሕይወቱን ለማትረፍ ከውስጥና ከውጭ በገንዘብ እርዳታ ቢረባረቡለትም በሞት የተጠቀለለውን የሕይወት እጥፋት ለመመለስ ግን ሳይቻል ቀረ፡፡ ጥር 4 ቀን 2016 ዓ.ም አጥቢያ እስትንፋሱ ተቋረጠ፡፡ ሥራውን ከእጹብ ማንነቱ ጋር ጥሎ፤ የሞትን እጥፋት ተከትሎ ሄደ፡፡

ሁለተኛው እጥፋት፤ ሁለተኛው ጥቁር ነጥብ በወርሀ ጥር፤ በሌላኛው የስፖርት ጋዜጠኛ ላይ ያረፈ ነበር፡፡ ገነነ መኩሪያ (ሊብሮ) ስምና ምግባር ልክክ ብለው ሲገጣጠሙ የመጀመሪያው ባይሆንም የመጨረሻውን ደረጃ ግን አሳይቷል፡፡ ልክ እንደ ስሙ ሁሉ ለራሱም ለሀገሩም ጀግና የነበረ ብርቱ የስፖርት ጋዜጠኛና ስፖርተኛ ለመሆን በ1955 ዓ.ም የመጋቢት ወር ላይ በይርጋለም ከተማ ተወለደ፡፡ የእርሱ የጋዜጠኝነት ሕይወት እንደ ዘንባባ ለምለምና ውብ ነበር አለማለት፤ ንፉግነት ነው፡፡ ምክንያቱም የእርሱ የጋዜጠኝነት ሕይወት የጀመረው አውቆና ተረድቶ በወጣትነት ሳይሆን፤ ምኑንም ከምኑ ለመለየት ከሚያዳግትበት ገና ከልጅነቱ ነበር፡፡ በሊጋ ዕድሜው ስፖርትና የስፖርት ጋዜጠኝነት አብረው በፍቅር ጣሉት፡፡ ይህም ፍቅር ከተወለደባት ይርጋለም እስከ ሻሸመኔ፤ ከሻሸመኔ እስከ አዲስ አበባና ምሥራቅ አፍሪካ በጎዳናዎቻቸው ሁሉ ስሙን እየተከለ በክብር አልፏል፡፡

ገና ታዳጊ የነበረው ገነነ፤ የስፖርት ጋዜጠኝነት ፍቅሩ ሲያናውዘው እንዲህ ነበር፡፡ ነጋዴው አባቱ መኩሪያ፤ በቁጥርና ፊደላት ያጨቁትን የሂሳብ መዝገባቸውን እያነሳ እርሱ ደግሞ በጽሑፍና ፎቶ ግራፍ ላይና ታቹን ያደማምቀዋል፡፡ ጋዜጦችን እያየ የራሱን ጋዜጣ እየሰራ መሆኑ ነው፡፡ ጋዜጣ በተለይ ደግሞ የስፖርት ጋዜጣ አያመልጠውም፤ እያደነ ከእጁ ያስገባቸዋል፡፡ ከዚያም በጋዜጣው ላይ ያሉትን ምስሎች ቀዶ እያወጣ ባዘጋጀው ወረቀት ላይ ይለጥፋቸዋል፡፡ የጋዜጦቹን ዜና እያነበበም በተረዳው መጠን የራሱን ዜና ይጽፍበታል፡፡ ቅሉ እርሱ ስም ባይሰጠውም `ገነነ ጋዜጣ' እንደማለት ነው፡፡ ይህን ጋዜጣ ከቤቱ ቁጭ አያደርገውም፤ እየወሰደ ለሠፈሩ ልጆች ግማሽ ገጽ ላነበበ የቁልፍ አዝራር፤ ሙሉውን ላነበበ ደግሞ አምስት ሳንቲም እያስከፈለ ያስነብባል፡፡

ሊብሮ የስፖርት ጋዜጠኛ ብቻ አልነበረም፡፡ ከዚያ ቀድሞ ራሱ ጎበዝ ስፖርተኛ ነበር፡፡ ከልጅነቱ ጀምሮ ይቺ ድቡልቡሏ ኳስ ለእርሱ ድቡልቡል ዓለሙ ናት። ኳሱን በእግሮቹ ባንቀሳቀሰ ቁጥር እሷኑ መሳይ የሆነችውን ይህቺን ድቡልቡል ዓለም፤ ከእግሮቹ በታች ያደረገ ያህል መስሎ ይሰማዋል፡፡ ምን አይነት ጸጋ ነው፤ምን አይነት መታደል እንዲሉ ከመኩሪያ ልጆች አምስቱ የእግር ኳስ ተጫዋቾች ነበሩ፡፡ ያውም በአንድ ቡድን ውስጥ፡፡ ታዳጊው ገነነና አራቱ ወንድሞቹ የሁሉንም ቀልብ የሳቡ ነበሩ፡፡ በአንድ ቤተሰብ የታጨቀውን የእግር ኳስ ቡድን የተመለከቱ አንዳንድ ሰዎች "የቡድኑ ስያሜ ተቀይሮ ለምን መኩሪያ ቡድን አይባልም" ይሉ እንደነበረ ገነነ በተለያዩ አጋጣሚዎች ያወሳዋል፡፡ በእግር ኳስ ሕይወቱ ከትንሿ የመንደር ጨዋታ ተነስቶ የኢትዮ ኤሌክትሪክና ሜታ ቢራን ጨምሮ በርካታ የእግር ኳስ ቡድኖችን ለመቀላቀል የቻለ ጀግና ነው፡፡ እንዲህ `ይታደሉታል እንጂ አይታገሉትም' የሚባለው ይሄው አይደል፡፡ "ሊብሮ" የሚለው የስሙ ስያሜም የፈለቀው ከዚሁ ነበር።

ከዕለታት በአንደኛው ቀን ይህ ሆነ፡፡ በጊዜው ገነነ(ሊብሮ) የሜታ ቢራ እግር ኳስ ቡድን ተጫዋች፤ ጓደኛው ኃይሌ ካሴ ደግሞ የቅዱስ ጊዮርጊስ ተጫዋች። ሁለቱም ቡድናቸውን ወክለው ወደሜዳ ሊገቡ የቀራቸው ጊዜ ከአንድ ሰዓት ያነሰ ነበር፡፡ እናም ሁለቱ ጓደኞች በመጨዋወት ላይ ሳሉ ገነነ መኩሪያ ሊብሮ ስለሚባል የእግር ኳስ ጥበብ ትንተና እየሰጠ ለወዳጁ ያጫውተዋል፡፡ ከዚያም ከወዳጅነቱ የአፍታ ጨዋታ፤ ሽሚያ ወደበዛበት ለእግር ኳስ ጨዋታ ወደ ሜዳው ገቡ፡፡ ጨዋታው ከተጀመረ ከደቂቃዎች በኋላ ቅድም ለጓደኛው ያጫወተው የሊብሮ ጥበብ ትዝ ቢለው፤ ከተከላካይ ስፍራ ላይ የነበረው ገነነ ለብቻው ኳሱን እየነዳ ከተቃራኒው የግብ ክልል ደረሰ፡፡ ከመድረሱም ከመረቡ ወዝውዞ ግሩም ግብ አስቆጠረ፡፡ ጓደኛውም አሁን በደንብ ሳይገባው አልቀረም፡፡ ገነነ ከጨዋታው መልስ "ሊብሮ" የሚል ቅጽል ስያሜ ተሰጠው። በዚህ ስም ከመታወቁም በላይ የኋላ በጋዜጠኝነቱ ወቅት ያዘጋጀው የነበረው የስፖርት ጋዜጣ ስምም ሆነ። ጋዜጣውም ለ13 ዓመታት ያህል ለመዝለቅ ችሏል። የግሉ ከነበረው ሊብሮ ባሻገርም ማራካኛ፣ ፉት ቦል፣ ሻምፒዮንና በሌሎች የስፖርት ጋዜጦች ላይም ሠርቷል፡፡

ከእግር ኳሱ ጉዳቶችና ድካም በኋላ ያመራው ወደየትም አልነበረም፤ ይልቅስ የልጅነት ህልሙ ወደነበረውና ወደጓጓለት የስፖርት ጋዜጠኝነት ሙያ ነበር፡፡ በጋዜጣ፣ በሬዲዮ፣ በቴሌቪዥን እንዲሁም በማህበራዊ የትስስር ገጾች ላይ ሳይቀር፤ ስፖርትን በጋዜጠኝነት ሙዳይ ውስጥ እንደያዘ 30 ዓመታትን ቆይቷል፡፡ በቅርቡም በአሻም የቴሌቪዥን መስኮት ብቅ ብሎ ስፖርቱን በመተንተን ላይ ነበር፡፡ ገነነ መኩሪያ ኳስን በእግር ማንጠባጠቡንና መተንተኑን ብቻም ሳይሆን፤ ብዕርን ከእጁ ማጥበቁንም ያውቅበታል። በእግር እየኮመኩ፤ በአፍ እየተነተኑ፤ በእጅ መከተቡ የእርሱ ናት፡፡ ስምንት መጽሐፍትን ጽፎ ለስፖርት አፍቃሪ አንባቢያንና ለሀገሩ አበርክቷል፡፡ ከጻፋቸው መጽሐፍት መካከል ኢህአፓ እና ስፖርት፣ ፍትሐዊ የጠጅ ክፍፍል እና መኩሪያ የተሰኙት ተጠቃሾች ናቸው፡፡ በርካቶች እንዲህ ሲሉ ነበር የሚጠሩት "ተንቀሳቃሹ ቤተ መጽሐፍት" በእርግጥም ነበረ። ሁለተኛው እጥፋትም እዚህ ጋር ነበር ጥር 14 ቀን 2016 ዓ.ም፡፡ በህመም ተይዞ ጉልበቱ ዛለና ሕክምና ሲደረግለት ቢቆይም፤ ከዚህች ቀን ንጋት ለማለፍ ግን ለማለፍ ሳይችል ቀረ፡፡ የዕድሜው ዘመን የተጻፈባት ያቺ ጦማር እጥፍ አለች፡፡ የሞት መልአክ ጦማሩን አጣጥፎ በቃህ አለው፡፡ ለሠራ ሰው ሞት ግዱም አይደል፤ ምክንያቱም ከሞት በላይ የሆነውን ሥራ ሰርቷልና። በእጥፋቱ ላይ፤ ሀገሩን እስቲ አንዲት ቃል ጻፊበት ብትባል፤ "ኮራሁብህ!" አሊያም "አመሰግንሀለሁ!" ነበር ሊሆን የሚችለው፡፡ ታዲያ ይህን ሰው እንዴትስ ሞተ ለማለት ይቻላል? ገነነ መኩሪያ ዕድሜ ዘመኑን ሙሉ ከስፖርት ጋር ኖሮ፤ ቢደክመው ጊዜ፤ በስፖርት ጥላ ስር አርፏል፡፡ የአፍሪካ እግር ኳስ ፌደሬሽን (ካፍ) ይህንን ውለታውን አልዘነጋውም፡፡ የክብር ሜዳይ ከአንገቱ አጥልቆለታል፡፡ ለዚህ ሽልማት ከበቁትም፤ ለአፍሪካ ስድስተኛው፤ ለምሥራቅ አፍሪካ ደግሞ ብቸኛው ሰው አድርጎታል፡፡ ኮምኮ ለግብ፤ ከትቦ ለንባብ...አይ ገነነ ...!!

እንግዲህ በወርሀ ጥር፤ ያውም በሳምንት ልዩነት እነዚህ ሁለት እንቁ ጋዜጠኞች የሕይወት ጦማራቸውን አስቀምጠውልን ሄደዋል፡፡ የወር ክፉ የለውምና `አንተ ክፉ' አይባልም፡፡ የቀንም ጎዶሎ የለምና `ጎዶሎ ቀን' አይባልም፡፡ የዕድሜ ውሃ-ልክ ሕይወትን አጣጥፎ፤ ሞትም መንገዱን እየጠቀለለ በማይፈታ እጥፋት ቢመጣ ነው፡፡ ነፍሳችሁን በአጸደ-ገነት ያኑረው ከማለት በስተቀር ምንስ ለማለት ይቻላል።



አስፋው መሸሻ ገነነ መኩሪያ

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



(በጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል።በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

# ሕግ እና የሕግ...

**ከገጽ 3 የዞረ**

ፍሬ ነገሮችን መሰረት ያደረገው የህግ የበላይነት እይታ አንድ ህግ ቅቡል ለመሆን ከሥነ ሥርዓታዊ መስፈርቶች በተጨማሪ የሞራል ቅቡልነት ያለው፣ ርትዕንና ሰብዓዊ መብቶችን እና ሌሎች ህገ መንግሥታዊ ድንጋጌዎችን ያከበረ መሆን ይገባዋል የሚል ነው።

የኢፌዴሪ ህገ መንግት በአንቀፅ 9 ማንኛውም ህግ፣ ልማዳዊ አሰራር እንዲሁም የመንግሥት አካል ወይም ባለስልጣን ውሳኔ ከዚህ ህገ መንግስት ጋር የሚቃረን ከሆነ ተፈፃሚነት እንደሌለው በመደንገግ በመንግስት ስልጣን ላይ ገደብ አስቀምጧል፡፡ ከዚህ ድንጋጌ የምንረዳው መንግሥት ምንም እንኳ ህጋዊ መስፈርቶችን ያሟላ ህግ ቢያወጣም ህገ መንግሥታዊ ድንጋጌዎችን ካላከበረ ህጉ ተፈፃሚነት የለውም። መንግሥት አላማውን ለማስፈፀም ወይም ለአገዛዝ እንዲመቸው መሰረታዊ ፍሬ ነገሮችን ያላከበረና መደበኛ የሕግ አወጣጥ ሥነ ሥርዓትን የተከተለ ህግ ሊያወጣ ይችላል፡፡

ለምሳሌ የደቡብ አፍሪካው አፓርታይድ ሥርዓት በህግ የተደገፈ ነበር፡፡ በሀገራችንም ፀረ ሽብር አዋጅ፣ የሲቪክ ማህበራት አዋጅ እና የምርጫ አዋጅ የገዢውን መንግሥት ስልጣን ለማራዘም ሲባል የዜጎችን ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶችን የሚገድቡ በመሆናቸው መንግስት የህግ የባላይነትን በሚያስከብር መልኩ እያሻሻላቸው ይገኛል፡፡ በመሆኑም የህግ የበላይነት ሲባል በህግ አውጪው አካል መደበኛ የህግ አወጣጥ ስነ ስርዓትን ተከትሎ በወጣ ህግ መተዳደር ብቻ ሳይሆን ህጉ ባስገዳጅ ሁኔታ ህገ መንግሥታዊ ድንጋጌዎችን ባከበረ መልኩ ስለመፅደቁ ትኩረት ይሻል ማለት ነው።

**የህግ የበላይነት ፋይዳ እና አላባውያን ምንምን ናቸው?**

የህግ የበላይነት የአስተዳደር መርህ ሲሆን ለሰላም ግንባታ፣ ለመልካም አስተዳደር፣ ለዘላቂ ኢኮኖሚያዊ ልማት እንዲሁም ውጤታማና ተአማኒነት ያለው የፍትህ አስተዳደር ተቋማት ለመገንባት በመሰረታዊነት የሚወሰድ ፅንሰ ሃሳብ ነው፡፡ በዋነኛነት ግን ሁለት መሰረታዊ ጉዳዮችን ለማሳካት የተወጠነ ሃሳብ ነው፡፡ እነሱም፡-የመንግሥትን የዘፈቀደ የስልጣን አጠቃቀምን ለመገደብ፣ የዜጎችን የንብረት፣ የነፃነት እና የሕይወት መብት በሌሎች እንዳይጣስ ጥበቃ ማድረግ ነው፡፡

በአንድ ሀገር መንግሥት ውስጥ የህግ የበላይነት ስለመኖሩ ማረጋገጭ የሚሆኑ መገለጫ አላባውያን የተለያዩ ቢሆኑም በአለም አቀፍ ደረጃ የህግ የበላይነትን የሚያከብሩ ሀገራትን ደረጃ(rule of law index) የሚያወጣው ዓለም አቀፉ የፍትህ ፕሮጅክት(world justice project) የሚጠቀምባቸውን መለኪያዎች ከህገ መንግሥታችን አኳያ የሚከተሉትን አምስት አላባውያን እናያለን፡፡

1.በህግ የተገደበ የመንግሥት ስልጣ
2.ህጋዊነት
3.ገለልተኛና ነፃ የዳኝነት አካል
4.ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች መከበር
**5.ሰላምና ደህነት**

በህግ የተገደበ የመንግሥት ስልጣን፡-

የመንግሥት፣ የባለስልጣናቱና እንደራሴዎቹ ሥልጣን መገደብ ወይም መወሰን አለበት የሚለው የህግ የበላይነት መለኪያ መስፈርት ከሁለት ሺ ዓመት በፊት ጀምሮ ሲያቀነቅኑት የነበረ ሲሆን ዋና አላማውም መንግሥት በዘፈቀደ ያለገደብ ልጓም እንደሌለው ፈረስ የሚፈነጭ ከሆነ የዜጎችን መብት በመጨፍለቅ ጨቋኝና አምባገነነ ይሆናል ተብሎ ስለሚታሰብ ነው፡፡ መንግሥት መጠቀም ያለበት የስልጣን መጠን የሀገርን እና የዜጎችን ሰላም፣ ደህንነት እና መብት አክብሮ ለማስከበር በሚያስችል መልኩ መሆን ይገባዋል። መንግስት በህግ የተሰጡትን ስልጣንና ተግባራት በሚፈፅምበት ወቅት በህግ በተቀመጡ አሰራሮች አግባብ መሆን ይገባዋል፡፡

ይህን ከተቃረነ በህግ ተጠያቂ ሊሆን ይገባል። በተጨማሪም ህጉን ለመቀየር ወይም ለማሻሻል ፍላጎት ቢያድርባቸው ህግ የማውጣት ስልጣንን የሚገድቡ ወሰኖችን(constraints) በመጣስ ሊሆን አይገባም፡፡ የኢፌድሪ ህገ መንግስት በአንቀጽ 9 ማንኛም ህግ፣ ልማዳዊ አሰራር፣ የመንግሥት አካል ወይም ባለስልጣን ውሳኔ ከዚህ ህገ መንግስት ጋር የሚቃረን ከሆነ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡ ከዚህ ድንጋጌ የምንረዳው ህግ አውጪው የሚያወጣው ህግ ወይም ሕግ አስፈፃሚው የሚወስነው ውሳኔ ወይም ህግ ተርጓሚው አካል ህግ ሲተረጉም ህገ መንግሥታዊ ድንጋጌዎችን ማክበር እንዳለበት በስልጣናቸው ላይ ገደብ አስቀምጧል፡፡

ይህን ገደብ የጣሰ ህግ፣ ውሳኔ እና የህግ ትርጉም ተፈፃሚነት የለውም፡፡ የመንግሥት አካላት በህግ በተሰጣቸው ስልጣን( separation of power) ብቻ እየሰሩ ስለመሆኑ ግልፅነትና ተያቂነት የሚያሰፍን የቁጥጥር ማድረጊያ መንገድ ሊኖር ይገባል፡፡ የኢፌዴሪ ህገ መንግስት በአንቀጽ 12 ማንኛውም ሃላፊና የህዝብ ተመራጭ ኃላፊነቱን ሲያጓድል ተጠያቂ እንደሚሆን ይደነግጋል። ቁጥጥርና ተጠያቂ ከሚደረግባቸው መንገዶች መካከል የሶስቱ የመንግሰት አካላት የእርስ በርስ ቁጥጥር መኖር( ለምሳሌ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 55(17-18) የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የአስፈፃሚውን አካል የሚቆጣጠሩበትን አግባብ ደንግጓል) ፣ ለሲቪል ማህበራትና ለሚዲያ ተጠያቂ በመሆን፣ የመንግስት ስልጣን በህግ አግባብ ብቻ እንዲተላለፍ በማድረግ(ህገ መንግስት አንቀጽ 9(3) ይመለከቷል) ወ.ዘተረፈ ይገኝበታል፡፡

**ህጋዊነት፡-**

የህግ የባላይነት ማረጋገጫ ከሚሆኑ ጉዳዮች መካከል አንዱ የህጋዊነት መርህ መኖር ሲሆን አንድ ህግ ከረቂቅ ጀምሮ ፀድቆ ተግባር ላይ በሚውልበት ወቅት ተደራሽ መሆኑ፣ ህጉ ግልፅና በቀላሉ የሚረዱት መሆኑ፣ ለውጥን የሚያስተናግድ፣ ተገማች የሆነ፣ ሊፈፀም የሚችል፣ በሁሉም ላይ በእኩል ተፈፃሚነት ያለው መሆኑ እና ማስፈፀሚ ሥርዓትና ተቋም ሊኖር ይገባል የሚል ነው፡፡ አንድ የህግ ሥርዓት እነዚህን መስፈርቶች የማያሟላ ከሆነ መንግሥት እና ዜጎች ለህጉ ይገዛሉ ተብሎ አይጠበቀም፡፡ ይህ መርህ መከበሩ ዜጎች ባልወጣ ህግ እንዳይቀጡና የወጡትንም ህጎች አክብረው የእለተ ተለት ህይወታቸውን እንዲመሩ ይደረጋል። ህጉም ተገማች በመሆኑ ግብይት እንዲሳለጥ ያደርጋል፡፡

ምክንያቱም ትርፍና ኪሳራቸውን አስልተው እንዲገበያዩ ያስችላቸዋል፡፡ ለምሳሌ የውል ህግ በመኖሩ ዜጎች ያለ ስጋት በነፃነት እንዲገበያዩ ዋስትና ይሰጣቸዋል። ውሉን ያላከበረ ተገዶ እንዲፈፅም ወይም ካሳ እንዲከፍል ስለሚደረግ ለሌላኛው ወገን ዋስትና ይሆናል፡፡ የንብረት ህግ ዜጎች ገንዘባቸውን፣ እውቀታቸውን እና ጉልበታቸውን አውጥተው ያፈሩትን ንብረት በነፃነት እንዲጠቀሙ ጥበቃ ያደርጋል። የዚህ መርህ መስፈርቶች ህገ መንግሥቱ ውስጥ ተደንግገው ይገኛሉ፡፡ ስለመንግስት አሰራር ግልፅነት እና ሁሉም ሰው በህግ ፊት እኩል መሆን በተመለከተ በሕገ መንግሥቱን አንቀጽ 12(1) እና 25 እንደቅደም ተከተላቸው ተደንግገዋል፡፡

**ገለልተኛና ነፃ የዳኝነት አካል፡-**

ነጻ የሆነ ፍ/ቤት የህግ በላይነት መሰረታዊ ገፅታና ለዲሞክራሲያዊ ሥርዓት መኖር ቅድመ ሁኔታ ነው። የዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ዋነኛው ባሕሪ ደግሞ የሰብዓዊ መብቶች መከበርና መረጋገጥ ነው። መሰረታዊ መብቶችና ነፃነቶች በሕገ-መንግሥት ወይም በሌላ ሕግ መደንገጋቸው ብቻ በራሱ ለመብቶች መረጋገጥ ዋስትና ሊሆን አይችልም። እነዚህ መብቶች እውን ይሆኑ ዘንድ ነፃ ፍ/ቤት መኖር አለበት፡፡ ነፃነት የሌለው ፍ/ቤት የሰዎችን መሰረታዊ ሰብዓዊ መብቶች እንዲረጋገጥ ሊያደርግ አይችልም፡፡

በዜጎችና በመንግሥት እንዲሁም በሰዎች መካከል ባሉ ግንኙነቶች ሳቢያ የሚነሱ የፍትሐብሔር ወይም ወንጀል ክርክሮችን ገለልተኛና ነፃ ሆኖ እልባት ሊሰጥ የሚችል ፍ/ቤት በሌለበት የሕግ በላይነት ሊረጋገጥ አይችልም። የህግ በላይነት ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ደግሞ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ እና መልካም አስተዳደር እውን ሊሆኑ አይችሉም፡፡ ሰላምና ዘለቄታ ያለው ልማትም ዋስትና አይኖረውም። የዳኝነት ነፃነት ለኢንቨስትመንትና ለኢኮኖሚ እድገት መሰረት ነው። ባለሀብቱ በፍርድ ቤቶች ላይ እምነት እንዲኖረው በአንድ ሀገር ውስጥ የዳኝነት ነፃነት መስፈንና መረጋገጥ ወሳኝ ነው፡፡

ስለዚህ ስለዳኝነት ነፃነት አስፈላጊነት ላይ ምንም ክርክር የለውም፡፡ የኢፌዴሪ ህገ መንግሥት በአንቀጽ 78 እና 79 ነፃ የዳኝነት አካል እንደተቋቋመ እና በየትኛውም ደረጃ የሚገኝ የዳኝነት አካል ከማንኛውም የመንግሥት አካል፣ ከማንኛውም ባለስልጣን ሆነ ከማንኛውም ሌላ ተፅእኖ ነፃ መሆናቸው እና ዳኞች የዳኝነት ተግባራቸውን በሙሉ ነፃነት በህግ በመመራት እንደሚያከናውኑ ተደንግጓል፡፡ ጥያቄው ያለው የዳኝነት ነፃነት ስፋትና እና ተግባራዊ አፈፃፀሙ ላይ ነው፡፡

**ሠላም፣ ሥርዓትና ደህንነት፡-**

የአንድ ሀገር መንግሥት፣ ህዝብና ነዋሪዎች ሰላም፣ ደህንነት፣ ሥርዓት መብትና ጥቅም መከበር እና መረጋገጥ የህግ የበላይነት ዋነኛ ገፅታ ነው፡፡ ዘላቂ ዋስትና ያለው ሰላም ለማረጋገጥ የሚቻለው በሀገራዊ ደህንነት፣ በመንግሥትና በህዝብ ጥቅም፣ በግለሰቦች ደህንነትና መብት ላይ የሚፈፀሙ የወንጀል ድርጊት ዝግጅቶችንና ሴራዎችን አስቀድሞ ለመከላከል ሲቻልና ወንጀሎቹ ከተፈፀሙ አጥፊዎችን በህግ ሥርዓት ተከታትሎ ለፍርድ ማቅረብና ለማስቀጣት ሲቻል ነው፡፡

የመንግሥት ባለስልጣናት፣ ፖለቲካ ድርጅቶች፣ የንግድ ድርጅቶች፣ ሌሎች ማህበራትና ማንኛውም ሰው የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴያቸውን በህገ መንግሥቱና ሌሎች የህግ ማዕቀፎችና ድንጋጌዎች መሰረት በማድረግ የማከናወን የዳበረ ባህል ሲዳብሩ የምርጫ ውድድሮች ጨምሮ ሌሎች ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካውና ማህበራዊ እንቅስቃሴዎች ህግና ሥርዓትን መሰረት በማድረግ የሚከናወኑ መሆን ይገባቸዋል፡፡ መንግሥት ሰላም እና ደህንነት ለማስጠበቅ ጉልበትን የመጠቀም(monopoly of coercive power) ብቸኛ መብት አለው፡፡

በመሆኑም ከህግ ከተፈቀደው ውጭ ዜጎች ወይም ሌሎች አካላት መብታቸውን ለማስከበር ኃይል የመጠቀም መብት የላቸውም፡፡ መንግሥት ሀገረ መንግሥቱ የቆመበትን ሥርዓትና ደህንነት ማስከበር አለበት ሲባል ወንጀል ከመፈፀሙ በፊት የመከላከል ሥራ መሰራት፣ ፖለቲካዊ ግጭቶችን(ሽብርተኝነት፣ አለመረጋጋትን፣ በታጠቁ ኃይሎች መካከል የሚደረግ ግጭትን) ውጤታማ በሆነ መልኩ መቀነስ እና የግል ችግርን ወይም በደልን ለመወጣት መደበኛውን የህግ ማስከበር ሥርዓት ከመከተል ይልቅ ኃይልን መጠቀም ማህበራዊ ተቀባይነት ያለው አድርጎ አለመፈፀም(ለምሳሌ የደቦ ፍትህ) በዋነኛነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

**ሰብዓዊ መብትና ነፃነቶች መከበር፡-**

ሰብዓዊ መብቶችና ነፃነቶች ከሰው ልጅ ተፈጥሮ የመነጩ የማይጣሱና የማይገፈፉ ናቸው፡፡ ሀገራችን ህገ መንግሥት የዜጎች ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች የሚከበሩ ስለመሆኑ በመሰረታዊ መርህነት የተደነገገ ከመሆኑም በላይ በማንኛውም ደረጃ የሚገኝ የፌዴራል መንግሥት የክልል ህግ አውጪ፣ አስፈፃሚና የዳኝነት አካል በህገ መንግሥቱ ምዕራፍ ሶስት በተካተቱ የሰብዓዊ መብትና መሠረታዊ ነፃነቶች ድንጋጌዎች የማክበርና የማስከበር ኃላፊነትና ግዴታ ያለባቸው ስለመሆኑ በአንቀጽ 13(1) ተደንግጓል። መንግሥት ሰብዓዊ መብቶችን የማክበርና የማስከበር ግዴታ የሚወጣው አስፈላጊውን የህግ፣ የአስተዳደርና ሌሎች እርምጃዎች በመውሰድ ነው፡፡

መንግሥት ከዜጎቹ ጋር ባለው የቀጥታ ግንኙነት እንዲሁም ዜጎች ባላቸው የእርስ በርስ ግንኙነት አንዱ የሌላውን መብት የማክበር ግዴታ አለበት፡፡ በመሆኑም የመንግሥት ባለስልጣናትና ሰራተኞች ስልጣንና ኃላፊነታቸውን አላግባብና ከህግ ውጪ በመጠቀም የሚፈፀሙትን የሰብዓዊ መብት ጥሰት ድርጊቶችን እንዲሁም ሰዎች ባላቸው የጎንዮሽ ግንኙነት አንዱ የሌላውን መብትና ነፃነት የሚጥሱ ድርጊቶች የወንጀል ተጠያቂነትና ኃላፊነት የሚያስከትሉ ድርጊቶች መሆናቸውን በመደንገግ፣ በመከላከል እና ጥሰቱ ተፈፅሞ ሲገኝ በተሟላ ሁኔታ በወንጀል ፍትህ ሥርዓቱ እንዲፈፀም በማድረግ መንግሥት ሰብዓዊ መብት የማክበርና የማስከበር ግዴታውን በመወጣት የህግ የባለይነትን ማረጋገጥ አለበት፡፡

**የህግ የበላይነትን ለማረጋገጥ ምን ይደረግ ?**

በአንድ ሀገር ውስጥ የህግ የበላይነት መኖር አማራጭ የሌለው ጉዳይ ነው፡፡ በአንፃራዊነት ካልሆነ በስተቀረ ከላይ የተመለከቱት የህግ የበላይነት መገለጫዎች ሙሉ በሙሉ የተከበረበት ሀገር የለም። የህግ የበላይነት በጊዜ ሂደት የሚገነባ እና የጋራ ባህል መገለጫ ይሆናል። መንግሥት እና ዜጎች ህጎች የእሴቶቻቸው መገለጫ እና ጥቅማቸውን ለማስከበር የወጡ መሆኑን ማመን አለባቸው፡፡ በመሆኑም እነዚህን ህጎች በማክበርም ሆነ በማስከበር የራሳቸውን ድርሻ መወጣት ይገባቸዋል፡፡

ሻሎም ! አሜን።

# ዓለም አቀፍ

## ትራምፕ በስም ማጥፋት ክስ 83 ነጥብ 3 ሚሊዮን ዶላር እንዲከፍሉ ተወሰነ

በጋዜጣው ሪፖርተር



ዶናልድ ትራምፕ በስም ማጥፋት ወንጀል ጥፋተኛ ተብለው 83.3 ሚሊዮን ዶላር ካሳ እንዲከፍሉ የዳኞች ስብስብ ፈረደባቸው።

ትራምፕ ፕሬዚዳንት ሳሉ እአአ በ2019 የጦማሪዋን ኢ. ጂን ካሮልን ስም አጥፍተዋል በሚል ነበር የተከሰሱት።

በ1990ዎቹ ኢ. ጂን ካሮል ላይ ወሲባዊ ትንኮሳ እንዳደረሱና ከዚያም ስሟን እንዳጠፉት በመግለጽ ክሱን ወደ ኒው ዮርክ ፍርድ ቤት ወስዳዋለች።

ክሱን እንዲሁም ብይኑን "ፈጽሞ የማይረባ" ሲሉ ትራምፕ አጣጥለዋል። ትራምፕ የሰጡት አስተያየት በስሜቷ እንዲሁም በበጎ ስሟ ላይ ያደረሰውን ጉዳት ፍርድ ቤቱ ተመልክቷል።

ከዚህ በኋላ ክፉ ነገር እንዳይናገሯት ማድረጊያ መንገድም በፍርድ ቤቱ ተነስቷል። ውሳኔው የተላለፈው ሰባት ወንድና ሁለት ሴት አባላት ባሉት ከሕዝብ በተውጣጡ ፍርድ ሰጪዎች (ጁሪ) ነው።

ውሳኔውን ተከትሎ ከሳሿ "ይሄ ለማንኛውም ጫና ለደረሰባትና አልሸነፍም ላለች ሴት ድል ነው። በጉልበት ተመክተው ሴቶችን ለመጨቆን የሚሞክሩ ደግሞ የተሸነፉበት ቀን ነው" ብላለች።

በዚህ ሂደት ላይ ተሳታፊ የነበሩ ከሕዝብ የተውጣጡ ፍርድ ሰጪዎች በክስ ሂደቱ ተሳታፊ መሆናቸውን ለሰዎች እንዳይናገሩ ተገልጾላቸው ነበር። ይህም ሊደርስባቸው የሚችለውን ጫና ከግምት በማስገባት ነው።

ከሳሿን አግተዋት እንደማያውቁና ከወንጀሉም ነጻ እንደሆኑ ትራምፕ ተከራክረዋል። "በውሳኔው አልስማማም። ባይደን በእኔ እና በሪፐብሊካን ፓርቲ ያቀነባበሩት ነው" ብለዋል ትራምፕ።

"የሕግ ሥርዓታችን መላ ቅጡን አጥቷል። እንደ ፖለቲካዊ መሣሪያ ጥቅም ላይ እየዋለ ነው። ይሄ አሜሪካ አይደለም" ሲሉም አክለዋል።

አምና በተካሄደ የፍርድ ቤት ክርክር ወሲባዊ ትንኮሳ እንዳደረሱባት ብይን ተሰጥቷል። ይሄኛው ደግሞ የስም ማጥፋትም እንዳደረሱባት ብይን የሰጠ ነው። ወሲባዊ ትንኮሳ እንደደረሰባት ስትገልጽ 'ውሸት ነው' በማለት ነው ስሟን ያጠፉት።

የትራምፕ ጠበቃ አሊና ሀባ ነበረች። በአንደኛው ቀን ፍርድ ቤቱን አቋርጠው ሊወጡ ሲሉ "እስር ቤት ልትገባ ትንሽ ነው የቀረህ። አርፈህ ተቀመጥ" ብላቸዋለች።

ዳኛውም ትራምፕ ሂደቱን እንዳያውኩ በተደጋጋሚ አስጠንቅቀዋል። ከፍርድ ቤት እንደሚያባርሯቸውም ገልጸው ነበር። የከሳሿ ጠበቃ "ይህ ሂደት ትራምፕን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ለማስቆም ያለመ ነው" ብለዋል።

ትራምፕ በአጠቃላይ 91 ክሶች አሉባቸው። በወንጀል በመከሰስ የመጀመሪያው የአሜሪካ ፕሬዝዳንትም ናቸው። ክሶቹ ግን በጆ ባይደን የተቀነባበሩ ናቸው ሲሉ በተደጋጋሚ ከሰዋል።

## የተመድ ባልደረቦች በሐማስ ጥቃት ተሳትፈዋል ተባለ

በጋዜጣው ሪፖርተር




የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት /ተመድ/ የፍልስጤም የእርዳታ ኤጀንሲ ባልደረቦች ከሐማስ ጋር በማበር በእስራኤል ላይ ድንገተኛውን ጥቃት ፈጽመዋል መባሉን ተከትሎ አሜሪካ ለተቋሙ ታደርግ የነበረውን የገንዘብ ድጋፍ አቋረጠች።

ተቋሙ ሠራተኞቹ በመስከረም 26ቱ ጥቃት ተሳትፈዋል መባሉን ተከትሎ በርካታ ሠራተኞቹን ማባረሩን እና ዝርዝር ምርመራ ለማድረግ ውሳኔ ማስተላለፉን አስታውቋል።

የተመድ ሠራተኞች በጥቃቱ ተሳትፈዋል የሚለውን መረጃ ያወጣችው እስራኤል ነች። ሠራተኞቹ በዚህ ጥቃት ላይ የነበራቸው ሚና ምን እንደሆነ አልተገለጸም።

የተመድ ዋና ጸሐፊ አንቶኒዮ ጉተሬዝ በጉዳዩ በጣም ማዘናቸውን ገልጸው ዝርዝር መርመራ ማዘዛቸውን ገልጸዋል።

የአሜሪካ መንግሥት የተመድ ሠራተኞች በዚህ የሐማስ ጥቃት ተሳታፊ ናቸው መባሉ እጅግ የሚረብሽ ዜና ነው ካለ በኋላ ለተቋሙ ይሰጥ የነበረውን የገንዘብ ድጋፍ በጊዜያዊነት ማገዱን አስታውቋል።

የተመድ የፍልስጤም የእርዳታ ኤጀንሲ ዋና ኃላፊ ፊሊፔ ላዛሪኒ እስራኤል ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ሠራተኞቻቸው በጥቃቱ ተሳታፊ መሆናቸውን የሚያመላክት መረጃ አቅርባለች ብለዋል። ይህ ተከትሎም ተቋሙ በበርካታ ሠራተኞች ላይ ምርመራ መጀመሩን ገልጸዋል።

የእስራኤል ጠቅላይ ሚንስትር አማካሪ የሆኑት ማርክ ሬጌቭ በመከስረም 26 ጥቃት ተሳታፊ ከነበሩት መካከል በተመድ የፍልስጤም እርዳታ ኤጀንሲ ደሞዝ የሚከፈላቸው ይገኙበታል ሲሉ ለቢቢሲ ተናግረዋል።

አማካሪው ጨምረውም በተመድ የፍልስጤም እርዳታ ኤጀንሲ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚሰሩ መምህራን በግልጽ የመስከረም 26ቱን ጥቃት በአደባባይ ሲያወደሱ ነበር ብለዋል።

ከዚህ በተጨማሪም ከእስራኤል ታግታ የነበረች አንዲት ሴት ከአገታ ከተለቀቀች በኋላ ታግታ የቆየችው ለተመድ በምትሰራ ሴት መኖሪያ ቤት ውስጥ መሆኑን ተናግራለች ብለዋል።

የተመድ ዋና ጸሐፊ አንቶኒዮ ጉተሬዝ የፍልስጤም እርዳታ ኤጅንሲ ኃላፊ ላዛሪኒ ጉዳዩን በጥልቀትና በፍጥነት እንዲመረምሩ ትዕዛዝ መስጠታቸውን አስታውቀዋል።

ዋና ጸሐፊው በመከስረም 26 የተሳተፉ ወይም የረዱ ሠራተኞችን ከሥራ ለማባረርና በተጨማሪም በወንጀል ለመክሰስ ምርመራ መካሄድ አለበት ብለዋል።

ጉተሬዝ ፈጣንና ጥልቅ የሆነ ምርመራ እንዲካሄድ መጠየቃቸውን አሜሪካ በአዎንታዊ መልክ እንምትወስደው አስታውቃለች።

የአውሮፓ ኅብረትም የሠራተኞቹን ተሳትፎ በሚመለከተው መረጃ እጅጉን ማዘኑን ገልጾ በጉዳዩ ላይ ተጨማሪ መረጃ ሲያገኝ እርምጃ እንደሚወስድ አስታውቋል። ለዚህ የተመድ ተቋም ከፍተኛ የገንዘብ ድጋፍ ከሚያደርጉ መካከል አሜሪካ፣ ጀርመን እና የአውሮፓ ኅብረት ተጠቃሽ ናቸው።

ኤጀንሲው በጋዛ፣ በዌስት ባንክ፣ ጆርዳን፣ ሶሪያ እና ሌባኖስ የሚገኙ ፍልስጤማውያንን የትምህርት፣ የጤና አገልግሎት እና የሰብዓዊ እርዳታ በማቅረብ ይረዳል።


አቢሲንያ ባንክ
Bank of Abyssinia

## ለአቢሲንያ ባንክ አ.ማ. ባለአክሲዮኖች በሙሉ

የአቢሲንያ ባንክ አ.ማ. የባለአክሲዮኖች 14ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ኅዳር 8 ቀን 2016 ዓ.ም. ባደረገው ስብሰባ የባንኩ ካፒታል ከብር 12.5 ቢሊዮን ወደ ብር 15 ቢሊዮን እንዲያድግ ወስኗል። አፈፃፀሙን በተመለከተም፡-

1. የባንኩን ካፒታል ወደ ብር 15 ቢሊዮን ለማሳደግ የሚወጡት ብር 2.5 ቢሊዮን ዋጋ ያላቸው ተጨማሪ አክሲዮኖች ለነባር ባለአክሲዮኖች ባላቸው የአክሲዮን ድርሻ መሠረት ተደልድሎ እንዲሸጥላቸው፣
2. ባለአክሲዮኖች የተመደበላቸውን የአዲስ አክሲዮን አጠቃላይ ዋጋ ¼ (25%) በን/ሕ/አንቀጽ 281 (1) መሠረት ወዲያውኑ በመክፈል ግዢ እንዲፈፅሙ እና ቀሪውን 75 በመቶ አክሲዮን ጠቅላላ ዋጋ እስከ ሚያዝያ 22 ቀን 2016 ዓ.ም. (እ.ኤ.አ. ኤፕሪል 30/2024) ድረስ ከፍለው እንዲያጠናቅቁ፣
3. ክፍያውም የዳይሬክተሮች ቦርድ በሚወስነው መሠረት ቀድመው ተፈርመው ያልተከፈሉ አክሲዮኖች ተጠናቀው ከተከፈሉ በኋላ ባሉት 30 ቀናት ውስጥ እንዲሆን፣
4. ባለአክሲዮኖች የተመደበላቸውን አክሲዮን ለመግዛት ሲቀርቡ ተጨማሪ አክሲዮን ለመግዛት ፈቃደኛ መሆናቸውንና የሚገዙትን አክሲዮን መጠን በሚዘጋጀው ፎርም ላይ በመሙላት እንዲያረጋግጡ፣
5. ባለአክሲዮኖች የተመደበላቸውን አክሲዮን ለመግዛት ፍላጐታቸውን ሳያሳውቁ ቀርተው ያልተሸጠ አክሲዮን ቢኖር በን/ሕ/አንቀጽ 449 መሠረት ተጨማሪ አክሲዮን ለመግዛት ሃሳባቸውን አስቀድመው በጽሑፍ ለገለጹ ባለአክሲዮኖች በወቅቱ ባላቸው መጠን በፕሮፖርሽን እንዲመደብላቸውና ግዢው ምደባው በተገለጸላቸው በ15 ተከታታይ ቀን ውስጥ እንዲጠናቀቅ፣
6. በዚህ ዙር አክሲዮን የገዙ ባለአክሲዮኖች የገዙትን አጠቃላይ አክሲዮን ዋጋ ¼ (25%) ወዲያውኑ በመክፈል ቀሪውን እስከ ሚያዚያ 22 ቀን 2016 ዓ.ም. ድረስ ከፍለው እንዲያጠናቅቁ፣
7. ከላይ በተጠቀሰው መሠረት ድልድል ተደርጐ በማናቸውም ምክንያት የተረፈ ቀሪ አክሲዮን ቢኖር፤ እንዲሁም አዲስ አክሲዮን ለመግዛት ፈርመው በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ከፍለው ያላጠናቀቁ ባለአክሲዮኖች ጉዳይ እና ሌላ ከአፈፃፀሙ ጋር ውሳኔ የሚጠይቅ ማናቸውም ጉዳይ የዳይሬክተሮች ቦርድ እንዲያስፈፅም ጉባዔው ወስኗል።


በመሆኑም በጉባዔው ውሳኔ መሠረት ባለአክሲዮኖች ከጥር 22 ቀን 2016 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ የካቲት 21 ቀን 2016 ዓ.ም. ድረስ ባሉት 30 ቀናት ውስጥ ለገሃር በሚገኘው የባንኩ ዋና መሥሪያ ቤት 8ኛ ፎቅ የአክሲዮንና ኢንቨስትመንት ክፍል በመቅረብ ግዢውን እንድትፈፅሙ እያሳወቅን፤ እስከ የካቲት 21 ቀን 2016 ዓ.ም. ድረስ የተመደበላቸውን አክሲዮን ለመግዛት ያልቀረቡና 25% ቅድመ ክፍያ ያልከፈሉ ባለአክሲዮኖች በጉባዔው ውሳኔ መሠረት በድልድል የሚደርሳቸው የአክሲዮን መጠን ተጨማሪ አክሲዮን ለመግዛት ፍላጐታቸውን ላሳወቁ ነባር ባለአክሲዮኖች በሚኖራቸው የአክሲዮን መጠን ተደልድሎ የሚተላለፍ መሆኑን አውቃችሁ በጊዜ ገደቡ ውስጥ የአክሲዮን ግዢውን እንድትፈፅሙ እናሳስባለን።

**ለተጨማሪ መረጃ በስልክ ቁጥር 011-552-6314 ደውለው መጠየቅ ይችላሉ።**

**አቢሲንያ ባንክ አ.ማ.**
**ዳይሬክተሮች ቦርድ**

**አዲስ አበባ**

# ስፖርት



## ‹‹ሊብሮ›› የኢትዮጵያ ስፖርት ቤተመጽሐፍት

ብርሃን ፈይሳ



ታሪክ አዋቂ፣ አንደበተ ርቱዕም ነው፡፡ በርካቶች ያለምንም ማስታወሻ በቀደመውን ዘመን የተፈጠሩ ጉዳዮችን አዋዝቶ ሲተርክ ያውቁታል። ላለፉት ዓመታት በራዲዮና ቴሌቪዥን መስኮቶች ከሚያዘጋጃቸው መርሀ ግብሮች ባለፈ እግር ኳሳዊና ማህበራዊ ጉዳዮችን እንዲተነትን እንዲሁም ባለፈው ጊዜ የሆነውን እንዲያስታውስ በበርካቶች ይጋበዛል። መረጃ ለሚጠይቀው የትኛውም ባለሙያ ተባባሪና በዘመናት የካበተ ዕውቀቱን ሳይሰስት ይሰጣል፡፡ በዕውቀት በተሞላ ማንነቱም በርካቶች ‹‹የኢትዮጵያ ስፖርት ቤተመጽሃፍት›› ይሉታል፡፡ ይህ ሰው ሰው ከቀናት በፊት በህወት የተለየን በተባ አንደበቱና ብዕሩ የኢትዮጵያን ስፖርት ለትውልዱ እንካችሁ የሚለው ጋዜጠኛው፣ የቀድሞ እግር ኳስ ተጫዋችና ሙዚቃ ወዳጁ ገነነ መኩሪያ ‹‹ሊብሮ›› ነው፡፡

የኢትዮጵያ ስፖርት እጅግ ከሚፈልጋቸው ሰዎች መካከል ሁለገብ ባለሙያው ገነነ በህመም ምክንያት ቢለየንም፤ በህይወት ሳለ አሻራውን ያሳረፈባቸው መጽሐፍትና ተረኮች ስሙን ከመቃብር በላይ ያውሉታል። በዛሬው የስፖርት ማህደር እትምም ይህንን የታሪክ ባለውለታ እናስታውሳለን። ገነነ የተወለደው መጋቢት 5/1957 ዓም ይርጋለም ከተማ ይሁን እንጂ ያደገው በሻሸመኔ ከተማ ነው፡፡ እግር ኳስን በሰፈር ቡድኖች የግብ ጠባቂ በመሆን ነበር የጀመረው፡፡ በአስደናቂ ጉዳዮች የታጀበ የተጫዋችነት ዘመኑን ገጠመኞች ሲያስታውስ ጥርስ የማያስከድነው ገነነ፤ በ1974 ዓም ከግብ ጠባቂነቱ በመውጣት የሜዳ ተጫዋች በመሆን አውራ ጎዳና ለተባለ ቡድን የወቅቱ ከፍተኛ ተከፋይ ሆኖ ተቀጠረ።

በአውራጃዎች ውድድር ያደገበትን የሻሸመኔን መለያ ለብሶ ሲሰለፍ፤ የሸዋ ውድድር ላይ ደግሞ ሀይቆችና ቡታጅራን ወክሎ ድንቅ ብቃቱን አሳይቷል። ይህ ችሎታው የ12ኛ ክፍል ተማሪ እያለ ለረጅም ጊዜ ለተጫወተበት ሜታ ቢራ እንዲፈርምም አድርጎታል። የክለቡ ተጫዋች ሆኖም 3 ጊዜ የኢትዮጵያ ሻምፒዮና እንዲሁም አንድ ጊዜ የብር ሜዳልያ ተሸላሚም ነበር። በተጫዋችነቱ ወቅት ግብ ጠባቂውን ጨምሮ አራት ተጫዋቾችን አልፎ ያስቆጠረው ግብ ተከትሎም እስከ እለተ ሞቱ ስሙን ተከትሎ የሚጠራበትን ‹‹ሊብሮ›› የሚል ቅጽል አትርፏል፡፡ ፈገግታን ከሚያጭሩና ለየት ካሉት የእግር ኳስ ገጠመኞቹ መካከልም በአንድ ዓመት ብቻ በራሱ ክለብ ላይ አምስት ግቦችን ያስቆጠረ ተጫዋች ነው፡፡

ገና በጠዋቱ ከስነ ጽሑፍ ጋር የተዋወቀው ገነነ ከመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት አንስቶ ስፖርታዊ ጉዳዮች ላይ መጻፍ ያዘወትር ነበር፡፡ ጋዜጣ በማዞር የሚያነባቸውን ታሪኮች መልሶ ለጓደኞቹ በመተንተንም ነበር ችሎታውን ያጎለበተው። ተጫዋች ሳለ በተግባረ ዕድ በጄነራል መካኒክነት ተምሮ የተመረቀ ሲሆን፤ ከዚሁ ጎን ለጎንም ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ ይጽፍ ነበር። ለሙያው ካለው ፍቅር የተነሳም ሌሎች በርካታ ጋዜጦች ላይ ያለ ክፍያም ነበር የሚጽፈው፡፡ ቆይቶም ሊብሮ ጋዜጣን አስጀመረ፡፡ በወቅቱ የስፖርት ቤተሰቡ በጉጉት ጠብቆ ከሚያነባቸው ተወዳጅ የስፖርት ጋዜጦች መካከል አንዱ በቅጽል ስሙ የተሰየመው ይኸው ጋዜጣ ነበር፡፡ ለ13 ዓመታት ለአንባቢያን ካደረሰ በኋላም የጋዜጣ ስራውን መጽሃፍ ወደማዘጋጀት ቀይሮታል። ከ30ዓመት በላይ በቆየበት የስፖርት ጋዜጠኝነት ህይወቱም ከጋዜጣ ባለፈ በሬዲዮ እንዲሁም በቴሊቪዥንም ሰርቷል፡፡

በጽሑፍ ችሎታው በርካቶችን ያስደመሙ መጽሐፍትን ባለፉት ዓመታት አሳትሟል፡፡ እውነተኛ ታሪክ ላይ የተመሰረተ ‹‹ኢህአፓና ስፖርት›› በሚል ርዕስ ከክፍል 1እስከ 3 ለአንባቢ ያደረሰው ገነነ በደርግ ዘመነ መንግስት ስፖርት(እግር ኳስ)፣ ወጣቶችና ፖለቲካ የነበሩበትን ሁኔታ በዝርዝር ያሳየበት ተወዳጅ መጽሃፍት ናቸው፡፡ የወቅቱን ሁኔታ ዋቢ ለማድረግ ከማስቻሉ ባለፈ ‹‹የነገን አልወልድም›› በሚል መጽሃፉን መነሻ ያደረገ ፊልምም እንደተሰራበት ይታወቃል፡፡ ሌላኛው በርካታ ፊልሞችን ሊያሰራ የሚችል ጉዳዮችን ያጠቃለለው መጽሃፉ ደግሞ ‹‹ፍትሃዊ የጠጅ ክፍፍል›› በሚል የታተመ ሲሆን፤ በአንባቢ ዘንድም የተወደዱ ናቸው፡፡ በንጉሳዊው ስርዓት ወቅት ታዋቂ ስለነበረውና ከንጉሱ ጋር የሚታየውን መኩሪያ የተባለ አንበሳ ታሪክ ያወሳበት ‹‹መኩሪያ›› የተባለ መጽሐፉም ታሪክን የኋሊት ዳሰሰበት ነው፡፡ ሊብሮ የራሱ የሆነ የእግር ኳስ ፍልስፍና ያለው ሲሆን፤ ‹‹ኢትዮጵያዊ ስልጠና›› በሚል ኢትዮጵያዊያን ታዳጊዎችን መሰረት ያደረገ የእግር ኳስ አሰለጣጠን ቴክኒክ ሊኖረው ይገባል በሚለው መልክ ያሳየበት ነው፡፡

ለዘመናት ለእግር ኳስ ስፖርት ላበረከተው ታላቅ አስተዋጽኦም በአዲስ አበባ ተሰናድቶ በነበረው የአፍሪካ እግር ኳስ ኮንፌዴሬሽን (ካፍ) ጠቅላላ ጉባኤ ላይ የረጅም ዘመን አገልግሎት ሜዳሊያ ተበርክቶለታል፡፡




## መጪውን ጊዜ ለቴክኖሎጂ

እየሩስ ተስፋዬ

ልጆችዬ እንዴት ናችሁ? ትምህርቱስ? ጥናት እንዴት ነው? በጣም ጥሩ እንደሚሆንላችሁ እተማመናለሁ፡፡ እንደምታውቁት ወይም እንደሰማችሁት በአሁኑ ወቅት ዓለማችን የቴክሎጂ ውጤቶችን በስፋት እየጠቀመች ትገኛለች፡፡ መጪዎቹ ዓመታትም ከዚህ ሊበልጡ እንጂ ሊቀንሱ ይችላል ተብሎ አይጠበቅም፡፡

ታዲያ ልጆችዬ እናንተስ ከቴክኖለጂው ጋር ለመተዋወቅ እና እንዴት መጠቀም እንዳለባችሁ ለመረዳት እየሞከራችሁ ነው? መልሳችሁ ‹‹አዎ›› እንደሚሆን ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ ስለዚህም ልጆችዬ ዛሬየምናቀርብላችሁሀገራችንኢትዮጵያንበመወከል ቻይና በተካሄደው ዓለም አቀፍ የሮቦቲክስ ውድድር ላይ ተሳትፎ ስላደረገው የኢትዮ ሮቦቲክስ ቡድን ይሆናል፡፡ ቡድኑ ሦስተኛ ደረጃን ይዞ አጠናቋል፡፡ በውድድሩ 21 ኢትዮጵያዊያን ታዳጊዎች የተወዳደሩ ሲሆን፤ በ“ቤስት ኦርጋናይዜሽን አዋርድ”፣ በ“ቤስት ቲም አዋርድ” እና በ“ሞስት ዲቨሎፕመንት አዋርድ” ለሽልማት በቅተዋል፡፡ የተወሰኑ ተሸላሚዎችን አነጋግረናል፤ ልምዳቸውን እና ተሞክሯቸውን እንደሚከተለው እንካፍላችኋለን፡፡

ተማሪ ኪሩብ ወንዱ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪ ነው፡፡ በቻይና ሀገር ሄደው ከተወዳደሩት ታዳጊዎች መካከል አንዱ ነው፡፡ በውድድሩ የእርሱ ድርሻም ሮቦቶችን ኮድ ማድረግ ነበር፡፡ ከተወዳደሩት 27 ሀገራት መካከል 3ተኛ በመውጣታቸው ደስታውን ይገልፃል፡፡

ተማሪ ኪሩብ ሀገራችን፣ ከቻይና እና ከሌች ሀገራት ጋር ስትወዳደር ገና በማደግ ላይ ያለች ሀገር እንደሆነች ከውድድሩ ተገንዝቧል፡፡ ስለዚህ ሀገራችን ጠንክራ መሥራት እንዳለባት ይመክራል፡ ፡ ልጆችዬ፣ ኪሩብ ወደ ፊት የሶፍትዌር ዲዛይነር መሆን ይፈልጋል፡፡ ለዚህ እንዲረዳውም ከትምህርቱ ጎን ለጎን የሮቦቲክስ ትምህርትን በመከታተል ላይ ነው፡፡

ለወደ ፊት ሰው ሠራሽ አስተውሎት (አትሪፊሻል ኢንተለጀንስ)ን የመጠቀሙ ነገር እንደሚስፋፋ ባለሙያዎች ይናገራሉ፡፡ እናም ኪሩብ ሀገራችን ቴክሎጂንየመጠቀሙነገርበሥፋትከተጠቀምችብት ካደጉት ሀገራት እኩል ለመሄድ እንደሚያግዛት ይናገራል፡፡ ስለዚህም፣ ልጆች ከቴክኖሊጂ ጋር ከተያየዙ ጉዳዮች ጋር ቅርርብናተገቢው እውቀት እንዲኖራቸው፤ የተለያዩ ስልጠናዎፐችንም እንዲወስዱ እመክራለሁ ብሏል፡፡

ወላጆች፣ ትምህርት ቤቶች፣ መምህራን፣ ለልጆች ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር ይጠበቅባቸዋል። መንግስትም ሮቦት እና ተያያዥ ትምህርቶችን እንደ አንድ የትምህርት ዓይነት ቢሰጡ ጥሩ ለውጥ ማምጣት እንደሚቻል ተማሪ ኪሩብ ይመክራል፡፡ የሂሳብ፣ ሳይንስ፣ ኢንጂነሪንግ እና መሰል ትምህርቶችን በመሠረታዊ ኮርስነት ቢሰጡ ሀገራችንን በቴክኖሎጂው ዘርፍ ለማሳደግ እንደሚረዳ ታዳጊው ይናገራል፡፡

ወደ ሌላኛው ተሳታፊ እና የማበረታቻ የምስክር ወረቀት ወደ ተሰጠው ተማሪ እንለፍ፡፡ ተማሪ አህመድ አቡበከር ይባላል፡፡ የ12ተኛ ክፍል የተፈጠሮ ሳይንስ ተማሪ ነው፡፡ ለወደፊት መካኒካል ኢኒጂነር የመሆን ፍላጎት አለው፡፡ አሁን የሚማረው የሮቦቲክስ ትምህርት ትልቅ እገዛ እንደሚደርግለት በመተማመን ከትምህርቱ ጎን ለጎን ስልጠናውን በመውሰድ ቻይና ሀገር ሄዶ ለመወዳደር በቅቷል፡ ፡ ለወደ ፊት በትምህርቱ ጠንክሮ በመማር ሀገሩን ለማገልገል ከፍተኛ ፍላጎት አለው፡፡

ቻይና ሀገር ሄደው ከመወዳደራቸው ባሻገር ብዙ ልምድ እንደቀሰመ የሚናገረው ተማሪ አህመድ፣ ከሶፍትዌር እና ሮቦቶችን ኮድ ከማድረግ ጋር በተያያዘ ብዙ ልምዶችን ማግኘቱንም ይገልጻል፡፡ ልጆችዬ፣ ተወዳዳሪው ተማሪ ለልጆች እና ለታዳጊዎች ምክር አለኝ ይላል፡፡ መጪውን ጊዜ በማሰብ ልጆች ከመደበኛ ትምህርታቸው በተጨማሪ ሳይንስ፣ ሂሳብ፣ ቴክኖሎጂ እና ኢንጂነሪንግን መማር አለባቸው የሚል ምክር ነው ያለው፡፡

ተማሪ ሄራኒ ፍቅሩን እናስተዋውቃችሁ። የአምስተኛ ክፍል ተማሪ ናት፡፡ ቻይና ሀገር ኢትዮጵያን ወክለው ከሄዱት መካከል አንዷ ናት። ለወደ ፊት ኢንጂነር የመሆን ፍላጎት ያላት ሲሆን፤ በርትታ ተምራ ሀገሯን የማስጠራት ፍላጎት እንዳለት ትናገራለች፡፡ ልጆች ከቴክኖሊጂ ጋር የተያያዙ ነገሮችን እንዴት መማር እና ማወቅ፤ የወላጅ እገዛ መጠየቅ እንዳለባቸውም ትመክራለች ፡፡

አቶ ሰናይ መኮንን የኢትዮ ሮቦቲክስ መሥራች እና ሥራ አስኪያጅ ናቸው፡፡ እርሳቸውም የአርቴፊሻል አስተውሎት (ኤአይ) ዓለምን እየተቆጣጠረ ያለ ቴክኖሎጂ እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ ስለዚህም ይህንን ታሳቢ በማድረግ ለልጆች ሮቦት እንዴት እንደሚሠራ በማሰልጠን ላይ ናቸው፡፡ ‹‹ልጆቻችን ዲዛይነሮች፣ ፕሮግራመሮች፣ እንዲሆኑ ስልጠና እየተሰጣቸው ነው›› ያሉ ሲሆን፤ ማዕከሉ በአሁን ሰዓት ከሁለት መቶ በላይ ተማሪዎችን እያሰለጠነ ይገኛል፡፡

አሁን ላይ ቴክሎጂ መር የሆነበት፤ ቴክኖሎጂ እየመራ ያለበት ዘመን ላይ ስለተደረሰ ህጻናት እና ታዳጊዎች ኢንጂነሮች፣ ዲዛይነሮች መሆን ይጠበቅባቸዋል ያሉት አቶ ሠናይ፣ በቅርቡ በየካቲት ወር፣ በአዲስ አበባ ከተማ የአፍሪካ ሻምፒዮን ይካሄዳል፡፡ ከተለያዩ የአፍሪካ ሀገሮች የሚመጡ ታዳጊዎች በዚህ ውድድር ላይ ይሳተፋሉ፡፡

አቶ ወንድሙ ሴታ የከተማ እና መሰረት ልማት ሚኒስቴር ዴኤታ እንዳሉት፤ ዓለም በቴክሎጂው ዘርፍ በፍጥነት እየሄደ ነው፡፡ ዓለም ላይ ለመድረስ ደግሞ ልጆች እና ታዳጊዎች የቴክኖሎጂ፣ ሂሳብ፣ ሳይንስ እና ኢንጂነሪንግ ግንዛቤ ሊያገኙ ይገባል፡፡ መንግሥትም ለልጆች ምቹ ሁኔታዎችን ለመፍጠር እየሠራ እንደሆነ አቶ ወንድሙ ገልጸዋል፡፡

ልጆችዬ፣ እነ ሄራኒ ጎበዞች ናቸው አይደል? እናንተም ጎበዞች ናችሁ። ስልክ ከመነካካት ይልቅ እንዴት ጌሞች እንደሚሠሩ እና መሰል ነገሮችን ለማወቅ መጓጓት ይኖርባችኋል፡፡ በሉ እንግዲህ ልጆችዬ፣ መሰነባበቻችን ደረሰ፡፡ በሌላ ቀን፣ በሌላ ርዕሰ ጉዳይ እስከምንገናኝ ቻው ቻው፡፡